**አዋጅ ቁጥር----/2012**

**<u>የግልግል ዳኝነትን እና የዕርቅ አሰራር ስርዓትን ለመደንገግ የወጣ አዋጅ</u>**

የግልግል ዳኝነትና የእርቅ አሰራር ስርአት መዘርጋቱ የአለመግባባት መፍቻ አማራጮችን በማስፋት ፍትህ የማግኘት መብትን ለማሟላት አጋዥ በመሆኑና በተለይም የኢንቨስትመንትና ንግድ ነክ አለመግባባቶችን ለመፍታት እና ለዘርፉ እድገት አስተዋፅኦ ያለው በመሆኑ፣

የግልግል ዳኝነት እና ዕርቅ የተዋዋይ ወገኖችን ወጪ በመቀነስ፣ ሚስጢርን በመጠበቅና ልዩ ሙያ ያላቸው ባለሙያዎች በዳኝነት እንዲሳተፉ በማድረግ እና ቀላልና ለተዋዋይ ወገኖች ነፃነት ያለው ሥነ ሥርዐት ለመጠቀም በመፍቀድ የተቀላጠፈ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል በመሆኑ፤

የሀገሪቱን ሁኔታ ታሳቢ በማድረግ በግልግል ዳኝነት የሚታዩ ጉዳዮችን ለመለየት፣ ሂደቱ የሚመራበትንና ውሳኔ የሚፈጸምበትን አጠቃላይ ማዕቀፍ መደንገግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

ኢትዮጵያ ተቀብላ ያጸደቀቻቸውን ዓለም ዓቀፍ ስምምነቶች ተግባራዊ ለማድረግ አጋዥ በመሆኑ፤

ከግልግል ዳኝነትና ከዕርቅ ጋር በተያያዘ የዳበሩ አለም አቀፍ አሰራሮችንና መርሆችን ታሳቢ በማድረግ በስራ ላይ ያሉ ሕጎችን ማሻሻል አስፈላጊ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**ክፍል አንድ**

**<u>ጠቅላላ</u>**

**1. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "የግልግል ዳኝነት እና የዕርቅ አሰራር ስርዓት አዋጅ ቁጥር ---/2012" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**2. <u>ትርጓሜ</u>**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1/ "የግልግል ዳኝነት ስምምነት" ማለት ከዉል ወይም ከዉል ዉጭ ባለ ሕጋዊ ግንኙነት ሊፈጠር የሚችልን ወይም የተፈጠረን አለመግባባት በሙሉ ወይም በከፊል በግልግል ዳኝነት ለመፍታት የሚፈፀም ስምምነት ነዉ፤

2/ "የግልግል ዳኝነት ውሳኔ" ማለት አለመግባባቶችን ለመፍታት በቋሚነት በተደራጀ የግልግል ተቋም ወይም በተዋዋይ ወገኖች ስምምነት በጊዜያዊነት በሚቋቋም የግልግል አካል የሚሰጥ ውሳኔ ነው፤

3/ "የግልግል ዳኝነት ማዕከል" ማለት በመንግስት ወይም በግል ባለቤትነት የሚቋቋም ሆኖ የግልግል ዳኝነት አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ነው፤

4/ “ፍርድ ቤት” ማለት መደበኛ የዳኝነት ሥልጣን ያለው በሕግ የተቋቋመ አካል ነው፤

5/ “ጉባዔ” ማለት አንድ ዳኛ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ዳኞች የሚሰየሙበት የግልግል ዳኞች ስብስብ ነው፤

6/ “የግልግል ዳኛ” ማለት በተዋዋይ ወገኖች ወይም በሦስተኛ ወገን የሚሰየም ገለልተኛ የሆነ የተፈጥሮ ሰው ነው፤

7/ “ንግድ ነክ” ማለት የንግድ ባህሪ ካላቸዉ ከዉል ወይም ከዉል ዉጭ ባሉ ግንኙነቶች ሁሉ የሚመነጩ ሆነው እቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን ለማቅረብ ወይም ለመለዋወጥ የሚደረግ የንግድ ግንኙነት፤ ለማከፋፈል የሚደረግ ስምምነት፤ የንግድወኪልነትን፤ ኪራይን፤ የግንባታ ስራን፤ የማማከር ስራን፤ የምህንድስና ስራን፤ ለንግድ ጉዳይ የሚደረጉ የፈቃድ ጉዳዮች፤ የኢንቨስትመንት፣ የፋይናንስ ስራ፤ የባንክ ስራ፤ ኢንሹራንስ ፤የማዕድንሥራዎች፣ በዚህ አዋጅ ከተከለከሉት ዉጭ ያሉ የአሽሙር እና ሌሎች ንግድ ማህበራት ጉዳዮች፤ በአየር በባህር ወይም በየብስ የሚደረጉ የሰዉ እና ዕቃ የማጓጓዝ ስራዎች እና የመሳሰሉትን ያካትታል፤

8/ “አስተዳደራዊ ዉል” ማለት በመንግስት በጀት በሙሉ ወይም በከፊል የሚተዳደር ተቋም ከማንኛውም ሰው ወይም ከሌላ የመንግስት ተቋም ጋር የሚደረግ ማንኛውም ውልን ይጨምራል፤

9/ “በውጭ ሀገር የተሰጠ የግልግል ዳኝነት ውሳኔ” ማለት ኢትዮጵያ ባፀደቃቻቸዉ አለም ዓቀፍ ስምምነቶች መሠረት በውጭ ሀገር እንደተሰጠ የሚቆጠር የግልግል ውሳኔን ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የግልግል ዳኝነቱ መቀመጫ በዉሳኔዉ ዉስጥ ከኢትዮጵያ ግዛት ዉጭ መሆኑ የተገለፀበት ዉሳኔ ነዉ፤

10/ “ዕርቅ” ማለት ሽምግልና፣ ዕርቅ ወይም ተመሳሳይ አገልግሎት የሚሰጥበትን ሂደት የሚያካትት ሆኖ፤ ዓላማው ዘላቂ መግባባት ላይ ለመድረስ በተዋዋይ ወገኖች ስምምነት አለመግባባቱ እንዲፈታ ለማስቻል በሚሰየም ሦስተኛ ወገን አማካኝነት የሚደረግ ሂደት ነው፤

11/ “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

12/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

1/ ኢትዮጵያ ፈራሚ የሆነችባቸዉ አለም አቀፍ ስምምነቶች እንደተጠበቁ ሆነው ይህ አዋጅ እንደ አግባብነቱ ንግድ ነክ በሆኑ ብሔራዊ ወይም አለም አቀፍ የግልግል ዳኝነቶች እና በዕርቅ በሚታዩ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፤

2/ አንድ የግልግል ዳኝነት ከዚህ በታች ከተመለከቱት በአንዱ ሥር የሚወድቅ ከሆነ አለም አቀፍ የግልግል ዳኝነት እንደሆነ ይቆጠራል፡-

ሀ) ተዋዋይ ወገኖች የግልግል ስምምነት በሚፈጽሙበት ወቅት ዋነኛ የቢዝነስ ቦታቸዉ በሁለት በተለያየ ሀገራት የነበረ ሲሆን፣

ለ) በግልግል ዳኝነት ስምምነቱ የተመረጠ የግልግል ዳኝነቱ ሕጋዊ መቀመጫ ወይም፣ በንግድ ወይም በዉል ግንኙነቱ ዉስጥ ያሉ ዋነኛ ግዴታዎች የሚፈፀሙባቸዉ ወይም አለመግባባቱ የተከሰተበትና የተያያዘበት የተዋዋይ ወገኖች ዋነኛ ቢዝነስ ቦታ ዉጭ ሀገር ሲገኝ፣

ሐ) ተዋዋይ ወገኖች የግልግል ዳኝነት ስምምነቱ ጉዳይ ከአንድ በላይ በሆኑ ሀገሮች የተያያዘ መሆኑን በግልፅ ሲስማሙ፡፡

3/ ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም ሲባል ተዋዋይ ወገኖች ከአንድ በላይ የቢዝነስ ቦታ ያላቸው ሆኖ ሲገኝ ለግልግል ስምምነቱ ቅርበት ያለዉ የቢዝነስ ቦታ እና ምንም የቢዝነስ ቦታ የሌላቸዉ ከሆነ የተዋዋይ ወገኖች መደበኛ መኖሪያ ቦታ እንደ ዋነኛ የቢዝነስ ቦታቸዉ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

## 4. የፍርድ ቤት ጣልቃ ገብነት

ፍርድ ቤቶች በዚህ አዋጅ ተለይቶ ከተሰጣቸው ሥልጣን በስተቀር፣ በግልግል ዳኝነት በሚታዩ ጉዳዮች ላይ ጣልቃ አይገቡም፡፡

**ክፍል ሁለት**

**የግልግል ዳኝነት ስምምነት**

## 5. የግልግል ዳኝነት ስምምነት ፎርም

1/ የግልግል ዳኝነት ስምምነት በጽሑፍ መሆን አለበት፤

2/ የግልግል ዳኝነት በጽሑፍ እንደተደረገ የሚቆጠረው በቃል፣ በድርጊት ወይም በሌላ አኳኋን የተደረገ ቢሆንም ይዘቱ ተመዝግቦ የሰፈረ፣ በሁሉም ተዋዋይ ወገኖች እና ሁለት ምስክሮች ሲፈረምበት ነዉ፤

3/ በኤሌክትሮኒክ መገናኛ ዘዴ የተደረገ የግልግል ስምምነት መረጃው በተፈለገ ጊዜ ጥቅም ላይ ለማዋል ተደራሽ ሆኖ የሚገኝ ከሆነ የጽሑፍ ፎርም እንዳሟላ ይቆጠራል፡፡ በኤሌክትሮኒክ፣ ማግኔቲክ ፣ ኦፕቲካል ወይም ተመሳሳይ በሆኑ ዘዴዎች ተዋዋይ ወገኖች የሚያደርጉት የኤሌክትሮኒክ፣ ኢሜይል፣ ቴሌግራም፣ ቴሌክስ እና ቴሌኮፒ መረጃ መልዕክት ልውውጥ እንደ ኤሌክትሮኒክ ግንኙነት ይቆጠራል፡፡

## 6. ለግልግል ዳኝነት የማይቀርቡ ጉዳዮች

የሚከተሉት ጉዳዮች ለግልግል ዳኝነት አይቀርቡም፡-

1/ የፍች፣ የጉዲፈቻ፣ የአሳዳሪነት ፣ የሞግዚትነት እና የውርስ ጉዳዮች፣

2/ የወንጀል ጉዳዮች፣

3/ የግብር ጉዳዮች፣

4/ መክሰር ላይ የሚሰጥ ውሳኔ፣

5/ የንግድ ማሕበራት መፍረስ ላይ የሚሰጥ ውሳኔ፣

6/ የሊዝ ጉዳይን ጨምሮ አጠቃላይ የመሬት ጉዳዮች፣

7/ አስተዳደራዊ ውሎች በልዩ ሁኔታ በሕግ ከተፈቀደ በስተቀር፣

8/ የንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ፤

9/ በሕግ ለሚመለከታቸው አስተዳደራዊ አካላት በተሰጠ ሥልጣን ሥር የሚሸፈኑ አስተዳደራዊ አለመግባባቶች

10/ በግልግል እንዳይታዩ በሕግ የተከለከሉ ሌሎች ጉዳዮች፡፡

**7. የግልግል ዳኝነት ስምምነት እና በፍርድ ቤቶች ስለሚቀርብ ክስ**

1/ በአንድ የግልግል ዳኝነት ስምምነት ዉስጥ በሚወድቅ አለመግባባት ላይ ለፍርድ ቤት ክስ ሲቀርብ እና ተከሳሹ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ተቃዉሞዉን ካቀረበ ፍርድ ቤት ክሱን ዉድቅ በማድረግ በግልግል ዳኝነት ስምምነቱ መሠረት ጉዳያቸዉን እንዲጨርሱ ሊያሰናብታቸዉ ይገባል፡፡

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ቢኖርም በሚከተሉት ምክንያቶች ፍርድቤት ጉዳዩን ለማየት ይችላል፡-

ሀ) የግልግል ዳኝነቱ ፈራሽ እና የማይፀና ከሆነ፣

ለ) የግልግል ዳኝነት ስምምነቱ ሊሰራበት የማይችል ወይም ለመፈፀም የማይቻል ሲሆን፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተጠቀሰዉ ክስ በፍርድ ቤት መጀመሩ እና በሂደት ላይ መሆኑ የግልግል ዳኝነቱን ጎን ለጎን ከመጀመር፣ ተጀምሮም ከሆነ ሂደቱን ከመቀጠል እና ጉባዔዉንም የግልግል ዳኝነት ዉሳኔ ከመስጠት አይከለክልም፡፡

**8. የግልግል ዳኝነት ስምምነት እና የመጠበቂያ እርምጃዎች**

የግልግል ዳኝነት ሂደቱ ከመጀመሩ በፊት ወይም በሂደት ላይ እያለ በግልግል ዳኝነት ስምምነት ዉስጥ ባሉ ተዋዋይ ወገኖች ጠያቂነት በግልግል ዳኝነት ስምምነት ዉስጥ በሚወድቁ ጉዳዮች ላይ ፍርድ ቤቶች የሚሰጡት የመጠበቂያ እርምጃ ትዕዛዝ ከግልግል ዳኝነት ስምምነት መንፈስ የሚቃረን ጣልቃ ገብነት አይደለም፡፡

**9. በግልግል ዳኝነት ስምምነት ላይ ተፈፃሚ ስለሚሆኑ ሕጎች**

1/ የግልግል ዳኝነቱ ስምምነትና ሂደቱ ተዋዋይ ወገኖች በመረጡት የግልግል ሕግ መሠረት ይታያል፤

2/ መቀመጫውን በኢትዮጵያ ባደረገ የግልግል ዳኝነት ስምምነት ላይ ተዋዋይ ወገኖች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ተፈፃሚ የሚሆነዉን ሕግ ያልመረጡ እንደሆነ ይህ አዋጅ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፤

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም፣ስምምነቱን በራሱ ለመፈጸም የማይቻል ሆኖ ሲገኝ ወይም የዚህን አዋጅ አስገዳጅ ድንጋጌዎችን የሚጻረር ሲሆን የተዋዋይ ወገኖች ስምምነት ተፈጻሚነት አይኖረውም፤

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት ተፈጻሚ ሊሆን የማይችል የተዋዋይ ወገኖች ስምምነት ሲያጋጥም ተዋዋይ ወገኖች በሚመርጡት ሌላ የግልግል ሕግ ወይም በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ግልግሉ ይታያል፡፡

## ክፍል ሦስት

## ስለ ግልግል ዳኞች ብዛት እና አሰያየም

**10. የግልግል ዳኞች ብዛት**

1/ ተዋዋይ ወገኖች የግልግል ዳኞቹን ብዛት በስምምነት መወሰን ይችላሉ፤ ሆኖም የዳኞቹ ብዛት ጎደሎ ቁጥር መሆን አለበት፤

2/ ተዋዋይ ወገኖች የዳኞችን ብዛት በስምምነት መወሰን ያልቻሉ እንደሆነ የግልግል ዳኞች ብዛት ሦስት ይሆናል፡፡

## 11. የግልግል ዳኞችን ስለመሰየም

1/ ተዋዋይ ወገኖች በሌላ መንገድ ካልተስማሙ በስተቀር ማንኛውም ሰው በዜግነቱ ምክንያት የግልግል ዳኛ ከመሆን ሊታገድ አይችልም፤

2/ በዚህ አዋጅ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር፣ ተዋዋይ ወገኖች በግልግል ዳኞች አሰያየም ሥነ ሥርዓት ላይ የመስማማት ነፃነት አላቸው፤

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ተዋዋይ ወገኖች ስምምነት ላይ ያልደረሱ እንደሆነ የሚከተሉት ተፈጻሚ ይሆናሉ፡-

ሀ) አንድ ዳኛ ብቻ ባለበት የግልግል ዳኝነት ሁለቱም ወገኖች በስምምነት ይመርጣሉ፤ ሦስት ዳኞች ያሉበት የግልግል ዳኝነት ላይ እያንዳንዱ ወገን አንድ ዳኛ ይመርጣል፤ሁለቱ የተመረጡ ዳኞች በሰብሳቢነት የሚሠራውን ሦስተኛ ዳኛ ይመርጣሉ፤

ለ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) የተደነገገው ቢኖርም፣ አንደኛው ወገን ዳኛ እንዲመርጥ በሌላኛው ወገን ማስታወቂያ በተሰጠው በሠላሳ ቀናት ውስጥ ዳኛ መምረጥ ካልቻለ ወይም ሁለቱም ዳኞች ከተመረጡ በሠላሳ ቀናት ውስጥ የሦስተኛ ዳኛ ምርጫ ላይ መስማማት ካልቻሉ ወይም አንድ ዳኛ ብቻ ባለበት የግልግል ዳኝነት ሁለቱም ወገኖች መስማማት ያልቻሉ እንደሆነ በአንደኛው ወገን ጠያቂነት የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት ዳኛውን ይሰይማል፤

ሐ) የግልግል ዳኝነት ሂደቱን የጀመረ ወገን ሌላኛዉ ወገን የግልግል ዳኛዉን በመምረጥ ሂደቱ እንዲሳተፍ ወይም በራሱ ወገን የሚመርጠዉን ዳኛ መርጦ እንዲያሳዉቅ በአግባቡ ማስታወቂያ ተሰቶት በሠላሳ ቀናት ዉስጥ ምላሽ ካልሰጠ ወይም የግልግል ዳኝነት ስምምነት መኖሩን የካደ እንደሆነ ጠያቂዉ አካል የግልግል ዳኝነት ስምምነቱን በራሱ ጊዜ የመሰረዝ እና ክሱን ለፍርድ ቤት የማቅረብ መብት ይኖረዋል፤

መ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ለ) መሠረት ፍርድ ቤቱ ዳኛ በሚመርጥበት ጊዜ በግልግል ስምምነቱ የተጠቀሱ መስፈርቶችን፣ የዳኛውን ገለልተኛነት ነፃነት እንዲሁም ከአለመግባባቱ ጋር በተያያዘ ያለዉን ሙያዊ ብቃት ከግምት ማስገባት አለበት፡፡

4/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ጉዳዩ የሚታየው በአንድ ዳኛ ብቻ በሚሆንበት ጊዜ ከላይ ከተገለፁት በተጨማሪ የግልግል ዳኛው ዜግነት ከተዋዋይ ወገኖች የተለየ ስለመሆኑ ከግምት ውስጥ መግባት አለበት፤

5/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (3) ፊደል ተራ (ለ) መሠረት በፍርድቤት የሚሰጠው ውሳኔ ይግባኝ አይቀርብበትም፡፡

## 12. የግልግል ዳኞች መብትና ግዴታ

1/ ማንኛውም ሰው ዳኛ እንዲሆን ጥያቄ ሲቀርብለት የጥቅም ግጭት፣ ገለልተኛነቱንና ነጻነቱን ሊያውክ የሚችል ወይም ምክንያታዊ ጥርጣሬ ሊያሳድር በሚችል ደረጃ የቤተሰብ፣ የብድር፣ የንግድ ወይም የንብረት ባለቤትነት ግንኙነት ከተዋዋይ ወገኖች ጋር ካለው ወይም ካጋጠመው ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት፤

2/ የግልግል ዳኛ ለስራው መሰየሙን የተቀበለ እንደሆነ መስማማቱን በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፤

3/ የግልግል ዳኛ የአገልግሎት ክፍያ የማግኘትና ላወጣው ወጪ የመካስ መብት አለው፤

4/ የግልግል ዳኛ ስራውን በቅልጥፍና መስራትና የግልግል ሂደቱ ያለአግባብ እንዳይራዘም ወቅቱን ጠብቆ እርምጃ መውሰድ አለበት፤

5/ ለግልግል በቀረበው ጉዳይ ላይ ጠበቃ፣ አማካሪ፣ አስማሚ ወይም በፍርድ ቤት ዳኛ በመሆን ከዚህ በፊት የተሳተፈ ሰዉ በዛው ጉዳይ ላይ የግልግል ዳኛ ሆኖ ማገልገል አይችልም፤

6/ በግልግል ሂደቱ አግባብ ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር ተዋዋይ ወገኖችን በተናጠል ማግኘት ወይም ከተዋዋይ ወገኖች ማንኛውንም ዓይነት ስጦታ መቀበል አይችልም፡፡

## 13. <u>የግልግል ዳኞችን ስለመቃወም</u>

1/ የአንድን ዳኛ መመረጥ መቃወም የሚቻለው ገለልተኛነቱን እና ነፃነቱን ወይም በግልግል ስምምነቱ ላይ የተቀመጡ መስፈርቶችን የማያሟላ መሆኑን አሳማኝ ጥርጣሬ ውስጥ የሚከቱ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ ብቻ ነው፤

2/ አንድ ወገን ራሱ በመረጠው ዳኛ ወይም በምርጫው ሂደት በተሳተፈበት ዳኛ ላይ ተቃውሞ ማቅረብ የሚችለው ዳኛው ከተመረጠ በኋላ በሚያውቀው ምክንያት ብቻ ነው፡፡

## 14. <u>የተቃውሞ ሥነ ሥርዐት</u>

1/ ተዋዋይ ወገኖች በግልግል ዳኞች ላይ ተቃውሞ ስለሚቀርብበት ሥነ ሥርዐት ስምምነት ማድረግ ይችላሉ፤

2/ በተዋዋይ ወገኖች የተደረገ ስምምነት የሌለ እንደሆነ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት በግልግል ዳኛ ላይ ተቃውሞ የማቅረብ ፍላጐት ያለው ወገን የግልግል ዳኛው ከተሰየመበት ወይም ለተቃውሞ ምክንያት የሆነውን ጉዳይ ካወቀበት ጊዜ አንስቶ በሚቆጠሩ አሥራ አምስት ቀናት ውስጥ ለመቃወም ምክንያት የሆነዉን ጉዳይ በጽሑፍ በመግለጽ ለጉባዔዉ ማቅረብ ይኖርበታል፤

3/ ተቃውሞ የቀረበበት ዳኛ በራሱ ፈቃድ ካልተነሳ ወይም ሌላኛው ወገን በተቃውሞው ካልተስማማ ጉባዔው በቀረበው ተቃውሞ ላይ ይወስናል፤

4/ ያቀረበው ተቃውሞ ውድቅ የተደረገበት ሰው ውጤቱ በተነገረው በሠላሳ ቀናት ውስጥ ለመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቅሬታዉን ማመልከት ይችላል፤ ፍርድ ቤቱ የሚሰጠው ውሳኔ ይግባኝ አይቀርብበትም፤

5/ ፍርድ ቤት በተቃውሞው ላይ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ የግልግል ዳኝነት ሂደቱ ታግዶ እንዲቆይ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

## 15. <u>ሥራን በአግባቡ ማከናወን አለመቻል</u>

1/ አንድ የግልግል ዳኛ በሕግ ወይም በሁኔታዎች ምክንያት ሥራውን በአግባቡ ማከናወን ካልቻለ ወይም ያለ በቂ ምክንያት ካዘገየ እና ተዋዋይ ወገኖች ከተስማሙ ከኃላፊነቱ ይነሳል፣ ተዋዋይ ወገኖች ይህንን ስምምነታቸዉን ለጉባዔዉ በጽሑፍ ማሳወቅ ይኖርባቸዋል፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ጉባዔው ርምጃ ካልወሰደ ወይም የግልግል ዳኛው በራሱ ፈቃድ ካልተነሳ ወይም ተዋዋይ ወገኖች ስምምነት ላይ ካልደረሱ ለመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ማመልከት ይችላሉ፣ ፍርድቤቱ የሚሰጠው ውሳኔ ይግባኝ አይቀርብበትም፤

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሠረት አንድ የግልግል ዳኛ ራሱን ከዳኝነት ማንሳቱ ወይም እንዲነሳ ተዋዋይ ወገኖች መስማማታቸው ዳኛው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተቀመጡ ሁኔታዎችን እንደተቀበለ አያስቆጥረውም፡፡

## 16. ተተኪ ዳኛ ስለመሰየም

1/ አንድ የግልግል ዳኛ በማንኛውም ምክንያት ከጉባዔ እንዲነሳ በመወሰኑ ወይም ራሱ ሥራውን በማቋረጡ ከኃላፊነቱ ሲሰናበት በምትኩ ሌላ ዳኛ ይሰየማል፤

2/ ተዋዋይ ወገኖች ተተኪ ዳኛ ስለሚሰየምበት ሁኔታ አዲስ ስምምነት ካላደረጉ በስተቀር፣ ተተኪ የግልግል ዳኛ የሚሰየመው የተቀየረው ዳኛ በተሰየመበት ሥርዓት ይሆናል፤

3/ በተነሱት የግልግል ዳኞች የታየው የግልግል ሂደት ካቆመበት እንዲቀጥል ወይም እንደ አዲስ ሂደቱ እንዲጀምር ተዋዋይ ወገኖች ሊስማሙ ይችላሉ፤ መስማማት ካልቻሉ ለመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት ሊያመለክቱ ይችላሉ፡፡

## 17. የግልግል ማዕከላት

1/ የግልግል ዳኝነት ማዕከል በመንግስት ወይም በግል ሊቋቋም ይችላል፤

2/ ጠቅላይ ዐቃቤሕግ የግልግል ማዕከላትን ይቆጣጠራል፣ ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፣የሚቋቋሙበትን መስፈርቶችን ያወጣል፤ ዝርዝሩ የሚኒስትሮች ምክርቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፤

3/ ይህ አዋጅ በስራ ላይ ያሉ የግልግል ዳኝነት ተቋማት እንዳይቀጥሉ አይከለክልም፡፡

## 18. ጉባዔው ሥልጣኑን በራሱ ስለመወሰኑ

1/ በተዋዋይ ወገኖች መካከል የፀና የግልግል ስምምነት መኖር አለመኖርን ጨምሮ ጉዳዮን የማየት ሥልጣን አለኝ ወይም የለኝም በሚለው ላይ ጉባዔዉ የመወሰን ሥልጣን አለው፣ ለዚህ ዓላማ ሲባል በአንድ ዋና ዉል ዉስጥ የተካተተ የግልግል ዳኝነት አንቀጽ ከዋናዉ ዉል እንደተለየ እና ራሱን እንደቻለ ዉል ይቆጠራል፣ የዋናዉ ዉል ፈራሽ እና ዋጋ የሌለዉ መሆን የግልግል ዳኝነት አንቀጹን ዋጋ እንዲያጣ እና ፈራሽ እንዲሆን አያደርገዉም፤

2/ በጉባዔው የሥረ ነገር ሥልጣን ላይ የሚነሳ ተቃውሞ ጉባዔው በፍሬ ነገር ላይ የሚያደርገውን ክርክር ከመስማቱ በፊት በመጀመሪያ ደረጃ ተቃውሞ መቅረብ አለበት፣ ተዋዋይ ወገኑ የግልግል ዳኛ በመምረጡ ወይም በሂደቱ በመሳተፉ ይህንን ተቃዉሞ ከማቅረብ አይከለከልም፤

3/ በጉባዔው በመታየት ላይ ያለው ጉዳይ ከግልግል ጉባዔው ሥልጣን በላይ ነው የሚል ተቃውሞ መቅረብ የሚገባው ከሥልጣን በላይ ነው የተባለው ጉዳይ መኖሩ እንደታወቀ መሆን አለበት፤

4/ ጉባዔው ዘግይቶ የቀረበን ተቃውሞ መቅረብ ያልቻለበት ምክንያት በቂ መሆኑን የተረዳው እንደሆነ ሊቀበለው ይችላል፤

5/ ጉባዔው በሥልጣኑ ላይ በሰጠው ውሳኔ ላይ ተቃውሞ የሚቀርበው ዉሳኔዉ በተሰጠ በአንድ ወር ጊዜ ዉስጥ ለመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይሆናል፤

6/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት ተቃውሞ መቅረቡ ጉባዔው በሂደት ላይ ያለውን የግልግል ዳኝነት ከመቀጠል እና ዉሳኔ ከመስጠት አያግደውም፡፡

## ክፍል አራት

## ስለ ጊዜያዊ መጠበቂያ እርምጃዎች

### 19. ጉባዔው ጊዜያዊ የመጠበቂያ እርምጃዎች ለማዘዝ ያለው ስልጣን

1/ ተዋዋይ ወገኖች በሌላ ሁኔታ ካልተስማሙ በስተቀር ተዋዋይ ወገን በሚያቀርው ጥያቄ መሠረት በግልግል ዳኝነት የቀረበውን ጉዳይ የሚመለከቱ ጊዜያዊ የመጠበቂያ እርምጃዎች መውሰድ ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው ጉባዔው ጊዜያዊ የመጠበቂያ እርምጃዎች ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚሰጥ ጊዜያዊ የመጠበቂያ እርምጃዎች ትዕዛዝ የሚከተሉትን ያካትታል፡፡

ሀ) አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎችን ለመጠበቅ፣

ለ) የክርክሩ አካል የሆኑ ዕቃዎች በተገቢ ሁኔታ እንዲጠበቁ ለማድረግ፣ በሦስተኛ ወገን ዘንድ እንዲቀመጡ ወይም የሚበላሹ ዕቃዎች እንዲሸጡ ለማድረግ ፣

ሐ) የግልግል ውሳኔ ሊያርፍባቸው የሚችሉ ሐብቶች እና ፈንዶች እንዲጠበቁ፣

መ) ለግልግሉ ምክንያት የሆነው አለመግባባት እስኪወሰን ድረስ የነበረው ሁኔታ እንዲቀጥል ወይም ወደነበረበት እንዲመለስ ለማድረግ፡፡

3/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ቢኖርም ጉባዔው በራሱ ተነሳሽነት የግልግል ዳኝነቱ ሂደትን ለማደናቀፍ የሚችል ወይም ጉዳት ለማድረስ የተቃረበ ጉዳይን እንዲቆም ለማድረግ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

### 20. ጊዜያዊ የመጠበቂያ እርምጃዎች ለመስጠት ከግምት የሚገቡ ሁኔታዎች እና ስለመያዣ

1/ ጉባዔው ጊዜያዊ የእርምጃ ትእዛዝ ለመስጠት ትዕዛዙ ባይሰጥ የማይካስ ጉዳት የሚደርስ ስለመሆኑ እና ትዕዛዙ የሚሰጥበት አካል ላይ የሚያደርሰው ተፅእኖ ተመዛዛኝነትን ከግምት ማስገባት ይኖርበታል፤

2/ ጉባዔው ትዕዛዙን በሚሠጥበት ጊዜ ለሌላኛው ወገን የመሰማት እድል መስጠት አለበት፤

3/ ጊዜያዊ የእርምጃ ትዕዛዝ እንዲሰጥ ጥያቄ ያቀረበው ተከራካሪ ወገን ትዕዛዙ ሊያስከትል የሚችለውን ኪሳራ የሚመጥን ዋስትና እንዲያቀርብ ጉባዔው ሊጠይቅ ይችላል፤

4/ ጉባዔው ትዕዛዝ እንዲሰጥለት ያቀረበው ወገን የተሰጠው ጊዜያዊ እርምጃ በወቅቱ በነበረው ሁኔታ ሊሰጥ አይገባውም ነበር ተብሎ ከታመነ ከጊዜያዊ ትእዛዙ ጋር በተያያዘ ለደረሰ ጉዳት ካሳ እንዲከፍል በተጨማሪነት ሊያዝ ይችላል፡፡

### 21. የቅድመ ጥንቃቄ ትዕዛዝ እንዲሰጥ ስለመጠየቅ

1/ ተዋዋይ ወገኖች በሌላ ሁኔታ ካልተስማሙ በስተቀር፣ ጊዜያዊ የመጠበቂያ እርምጃዎች እንዲሰጡለት ጥያቄ ያቀረበ ተዋዋይ ወገን ሌላኛውን ወገን ሳያሳውቅ በተጓዳኝ የመጠበቂያ እርምጃዎችን ተግባራዊነት እንዳያደናቅፍ የቅድመ ጥንቃቄ ትዕዛዝ እንዲሰጥለት ጉባዔውን ሊጠይቅ ይችላል፤

2/ ጉባዔው ለሌላኛው ወገን ማሳወቁ ትዕዛዙ እንዳይፈፀም ያደርጋል ብሎ በበቂ ሁኔታ ሲያምን ሌላኛውን ወገን ሳያሳውቅ ትዕዛዙን ሊሰጥ ይችላል፤

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ጉባዔው የሰጠውን የቅድመ ጥንቃቄ ትዕዛዝ ሌላኛውን ወገን ከሠማ በኋላ ትዕዛዙን ሊያሻሽል፣ ሊያፀና ወይም ሊሽር ይችላል፡፡

## 22. ጊዚያዊ የመጠበቂያ እርምጃ ትዕዛዞችን ስለማሻሻል፣ ለጊዜው ስለማገድ እና መሰረዝ

ጉባዔው በተዋዋይ ወገኖች ጥያቄ ወይም በልዩ ሁኔታ ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው ለተዋዋይ ወገኖች በማሳወቅ በራሱ ተነሳሽነት የሰጠውን ትዕዛዝ ለጊዜው ሊያሻሽል፣ ሊያግድ፣ ወይም ሊሰርዘው ይችላል፡፡

## 23. ስለማሳወቅ

1/ ከተሠጠው የቅድመ ጥንቃቄ ወይም ጊዚያዊ የመጠበቂያ እርምጃ ትዕዛዝ ጋር ተያይዞ የተደረጉ ለውጦች ሲኖሩ ተዋዋይ ወገን ወዲያውኑ ለጉባዔው እንዲያሳውቅ ጉባዔው ሊያዝ ይችላል፤

2/ ቅድመ ጥንቃቄ ትዕዛዝ እንዲሰጥለት ጥያቄ ያቀረበ ተዋዋይ ወገን ሌላኛው ወገን ቀርቦ እስኪያስረዳ ድረስ የቅድመ ጥንቃቄ ትዕዛዞችን ለመስጠት ወይም ለማስቀጠል መነሻ የሆኑ ማናቸውንም የሁኔታዎችን ለውጥ ለጉባዔው የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

## 24. ለጊዚያዊ የመጠበቂያ እርምጃ ትዕዛዝ እውቅና ስለመስጠትና ስለማስፈጸም

1/ የውጭ ፍርዶችን እውቅና ስለመስጠትና አፈጻጸምን በተመለከተ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የተሰጠበትን ሀገር ከግምት ሳያስገባ በጉባዔ የተሰጠ ጊዚያዊ እርምጃ ትዕዛዝ አስገዳጅነት ይኖረዋል፤

2/ ጊዚያዊ የመጠበቂያ እርምጃ ትዕዛዝ መፈፀም ካልቻለ አንደኛው ወገን ትዕዛዙ እንዲፈፀምለት ለፍርድ ቤት ሊያመለክት ይችላል፤

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ጥያቄ የቀረበው ከሀገር ውስጥ ከሆነ ጉዳዩ ለግልግል ዳኝነት ባይቀርብ ኖሮ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ላለው ፍርድቤት ይቀርባል፣ ትዕዛዙ በውጭ ሀገር በሚገኝ የግልግል ዳኝነት የተሠጠ ከሆነ ጉዳዩን የማየት ሥልጣን የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይሆናል፤

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት ጥያቄ የቀረበለት ፍርድ ቤት ጉባዔው በዋስትና ላይ ባልወሰነ ጊዜ እና ጊዚያዊ የመጠበቂያ እርምጃ እንዲፈጸምለት የሚጠይቀውን ወገን ወይም የሦስተኛ ወገኖችን ጥቅም ለማስጠበቅ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ዋስትና እንዲያቀርብ ሊጠይቅ ይችላል፣ የቀረበው ጥያቄ ለሌላኛው ተዋዋይ ወገን እንዲደርሰው መደረግ አለበት፤

5/ ጊዚያዊ የእርምጃ ትዕዛዝ እንዲፈጸምለት ለፍርድ ቤት ያቀረበ ተዋዋይ ወገን በጉባዔው የተሰጠውን ትዕዛዝ አስመልክቶ የተደረገ ማንኛውም መሻሻል፣ ጊዚያዊ እግድ ወይም መሰረዝ ለፍርድ ቤቱ ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

## 25. ጊዚያዊ የመጠበቂያ የእርምጃ ትዕዛዝ ጥያቄን በፍርድ ቤት ስላለመቀበል

1/ ፍርድ ቤት ጊዚያዊ እርምጃ ትዕዛዞችን በተመለከተ እውቅና እንዲሰጥ ወይም እንዲፈጸም የቀረበውን ጥያቄ የሚከተሉትን ምክንያቶች መሠረት በማድረግ ላለመቀበል ይችላል፡-

ሀ) ፍርድን ላለመቀበል የተመለከቱት ድንጋጌዎች በተለይ የተዋዋይ ወገን ችሎታ ማጣት፣ የጸና የግልግል ስምምነት አለመኖር፣ ለትዕዛዝ ምክንያት የሆነው ጉዳይ በግልግል ዳኝነት የማይታይ ከሆነ ወይም ጉባዔው ስልጣን የሌለው ከሆነ ወይም ትዕዛዙ ጉባዔው ከተሰጠው ስልጣን በላይ ከሆነ ወይም፣

ለ) መያዣን አስመልክቶ በጉባዔው የተሰጠው ውሳኔ ያልተከበረ እንደሆነ፣

ሐ) ጊዚያዊ የመጠበቂያ እርምጃዎቹ በተመለከተ የተሰጠው ውሳኔ የተሻሻለ፣ በጊዚያዊነት የታገደ ወይም የተሰረዘ እንደሆነ፣

መ) ፍርድ ቤቱ ስልጣን የሌለው ሆኖ ሲያገኘው ወይም ፣

ሠ) የጊዚያዊ መጠበቂያ እርምጃ ትዕዛዙን መቀበል ወይም ማስፈጸም ለሕዝብ ሞራልና ፖሊሲ ጋር የሚቃረን ሆኖ ሲያገኘው፡፡

2/ ትዕዛዙ እንዲፈፀምለት የቀረበበት ፍርድ ቤት ከላይ የተመለከቱትን ምክንያቶች በመወሰን ሂደት የጊዚያዊ የመጠበቂያ እርምጃ ትዕዛዙን ይዘት መከለስ አይችልም፡፡

**26. <u>በፍርድ ቤት ስለሚሰጡ ጊዚያዊ የመጠበቂያ እርምጃዎች</u>**

የግልግል መቀመጫው በየትኛውም ቦታ ያደረገ የግልግል ዳኝነት ከግምት ሳይገባ ተዋዋይ ወገኖች የጊዚያዊ መጠበቂያ እርምጃ ትዕዛዝ እንዲሰጥላቸው ፍርድቤት ሊጠይቁ ይችላሉ፡፡

## ክፍል አምስት

## <u>ስለ ግልግል ዳኝነት ሂደት</u>

**27. <u>ተዋዋይ ወገኖችን በእኩል ስለመስማት</u>**

ሁሉም ባለጉዳዮች እኩል የመስተናገድ ፣ ጉዳያቸዉን የማቅረብ እና የመሰማት መብት ሊሰጣቸዉ ይገባል፡፡

**28. <u>ሥነ ሥርዐት ስለመወሰን</u>**

1/ በዚህ አዋጅ የተደነገጉ አስገዳጅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ተዋዋይ ወገኖች ጉባዔው ሊከተለው የሚገባውን ሥነ ሥርዓት በስምምነት ሊወስኑ ወይም በሦስተኛ ወገን እንዲወሰን ሊስማሙ ይችላሉ፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በስምምነት የተወሰነ ሥነ ሥርዓት ከሌለ ጉባዔው ተገቢ ነው ብሎ ያሰበውን ሥነ ሥርዐት ይወስናል፤ ሥነ ሥርዐትን ስለመወሰን ለጉባዔው የተሰጠው ሥልጣን የማስረጃ ተቀባይነት፣አስፈላጊነት እና ምዘናን የተመለከቱ ጉዳዮችን ይጨምራል፡፡

**29. <u>የጉባዔው መቀመጫ ቦታ</u>**

1/ ተዋዋይ ወገኖች የግልግል ዳኝነቱ የሚካሄድበትን በሕግ አግባብ የግልግል ዳኝነት መቀመጫ ተብሎ የሚጠራዉን ቦታ በስምምነት መምረጥ ይችላሉ፤

2/ ተዋዋይ ወገኖች የግልግል ዳኝነት የሚካሄድበትን ቦታ በስምምነት መምረጥ ካልቻሉ የግልግል ዳኝነት ጉባዔው ለጉዳዩ አግባብነት ያለዉን መቀመጫ መወሰን አለበት፤

3/ ተዋዋይ ወገኖች በሌላ አኳኋን ካልተስማሙ በስተቀር፣የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ቢኖሩም፣ ለምክክር፣ የምስክርን ቃል ለመስማት፣ የባለሙያዎችን ቃል ለመቀበል፣ ንብረቶችንና ሰነዶችን ለመመርመር ወይም ተያያዥ የሆኑ ሌሎች ተግባራትን የግልግል ዳኝነት ጉባዔው እንደአስፈላጊነቱ በሌላ ቦታ ሊያከናዉን ይችላል ፡፡

## 30. <u>የግልግል ዳኝነት ስለመጀመርና ስለማሳወቅ</u>

1/ ተዋዋይ ወገኖች በሌላ ሁኔታ ካልተስማሙ በስተቀር የግልግል ዳኝነት ሂደቱ የተጀመረበት ቀን ተብሎ የሚታሰበው ከሳሽ ክርክሩን ለግልግል ዳኝነት ለመምራት እንደወሰነ የሚገልፅ ጥያቄ ለተከሳሽ ከደረሰበት ቀን ጀምሮ ነው፤ የግልግል ዳኝነት ጥያቄዉ በጽሑፍ ሆኖ የተዋዋይ ወገኖችን ስም፣ ለግልግል ዳኝነት ምክንያት የሆነዉን አለመግባባት እና መነሻ የሆነዉን የግልግል ስምምነት የሚያጣቅስ መሆን አለበት፤

2/ የግልግል ዳኝነት ጥያቄው የደረሰው ተዋዋይ ወገን የግልግል ዳኝነት መኖር አለመኖሩን፣ስለ አለመግባባቱ ፣ በግልግል ዳኝነት ለመቀጠል ያለውን ፍላጎት በ30 ቀን ውስጥ በጽሑፍ ምላሹን ማቅረብ አለበት፤

3/ የግልግል ዳኝነት ጥያቄ የቀረበለት ተዋዋይ ወገን የግልግል ዳኝነት ስምምነት መኖሩን ከካደ ፣ በግልግል ዳኝነት ለመቀጠል ፍላጎት የሌለው መሆኑን ከገለፀ ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ መልስ ካልሰጠ ጥያቄ አቅራቢው ወገን ጉዳዩን ለፍርድቤት የማቅረብ መብት ይኖረዋል፤

4/ ተዋዋይ ወገኖች በመረጡት ሰው ወይም በጠበቃ መወከል ይችላሉ፤ የግልግል ዳኝነት ሂደትን በወኪል ማከናወን የፈለገ ወገን የሚወክለውን ሰው ስምና አድራሻ የያዘ ማሳወቂያ ለሌላኛው ወገን እና ለጉባዔው መላክ አለበት፤

5/ በተዋዋይ ወገኖች የተለየ ስምምነት ከሌለ በስተቀር፣ የግልግል ዳኝነት የክስ መጥሪያን እና ማንኛውም ማስታወቂያ በሚከተሉት አማራጮች የሚደርስ ይሆናል፡-

ሀ) ማንኛውም የፅሑፍ ማስታወቂያ ለተቀባዩ ወይም ለሕጋዊ ወኪሉ በአካል ከተሰጠ ፣በስራው ወይም በመደበኛ መኖሪያ ቦታው ከደረሰ ፣ ተዋዋይ ወገኖች በሚገለገሉበት ወይም በግልግል ዳኝነት ስምምነታቸው ወይም በዋናው ውል ውስጥ በተጠቀሰው የኢሜይል አድራሻ የተላከ እንደሆነ ማስታወቂያው እንደደረሰ ይቆጠራል፤

ለ) በዚህ አንቀፀ ንዑስ አንቀፀ 5 ፊደል ተራ ሀ መሰረት ለተዋዋይ ወገን ማስታወቂያ ወይም መጥሪያ እንዲደርስ ለማድረግ ተገቢው ጥረት ተደርጎ ማግኘት ያልተቻለ እንደሆነ ተዋዋይ ወገን በመጨረሻ ይኖርበት በነበረበው መደበኛ የመኖሪያ ቦታ ወይም ንግዱን በሚያከናውንበት አድራሻ በመላክ ወይም ይጠቀምበት በነበረው የፖስታ ፣ ኢሜይል ፣በመልዕክተኛ ከተላከ ወይም ማስታወቂያ ወይም መጥሪያው በጽሑፍ መድረሱን ለማሳየት በሚቻልበት ማናቸውም መንገድ ከተላከ ማስታወቂያ ወይም መጥሪያ እንደደረሰ ይቆጠራል፤

ሐ) ተቀባዩ ማስታወቂያውን ወይም መጥሪያውን ለመቀበል ፈቃደኛ አለመሆኑን ወይም መድረሱን ለመግለፅ እምቢተኝነቱን የግልግል ጉባዔው ካረጋገጠ ተቀባይ መጥሪያው እንደደረሰው ተቆጥሮ በሌለበት ክርክሩ እንዲቀጥል ያደርጋል፡፡

6/ የጊዜ ገደብን ለማስላት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) በተመለከቱት አማራጮች መሠረት የደረሰ መጥሪያ ወይም ማስታወቂያ ቀን መቁጠር የሚጀምረው መጥሪያው ከደረሰበት ወይም ማስታወቂያው ከተሰጠበት ቀጥሎ ባለው ቀን ይሆናል፡፡

## 31. <u>ቋንቋ</u>

1/ ተዋዋይ ወገኖች በግልግል ዳኝነት ሂደት ስለሚጠቀሙበት ቋንቋ በስምምነት ሊወስኑ ይችላሉ፤

2/ ተዋዋይ ወገኖች በቋንቋ ምርጫ መስማማት ካልቻሉ ጉባዔው አግባብነት ያለውን ቋንቋ ይወስናል፤

3/ ጉባዔው የሰነድ ማስረጃዎች በተዋዋይ ወገኖች ስምምነት ወይም በጉባዔዉ ዉሳኔ መሠረት በተመረጠው ቋንቋ ወይም በተመረጡት ቋንቋዎች ተተርጉሞ እንዲቀርብ ማዘዝ ይችላል፤

4/ ተዋዋይ ወገኖች ያደረጉት የተለየ ስምምነት ከሌለ በስተቀር የግልግል ዳኝነት ጉባዔውን የሥራ ቋንቋ ለማይችል ተዋዋይ ወገን፣ ምስክር ወይም ልዩ አዋቂ በሚረዳው ቋንቋ ወይም በምልክት እንዲተረጎምት አስተርጓሚ ይመደብለታል፡፡

## 32. <u>ስለ ክስ ማመልከቻ እና የመከላከያ መልስ</u>

1/ የክስ ማመልከቻ የግልግል ዳኝነት ስምምነቱን ድንጋጌ በማጣቀስ የከሳሽና የተከሳሽ አድራሻን፣የክሱን አቤቱታና የሚደግፉትን ፍሬነገሮች እና ከሳሽ የሚጠይቃቸውን ዳኝነቶች በማካተት ከደጋፊ ማስረጃዎች ጋር መቅረብ ይኖርበታል፤

2/ የክስ ማመልከቻው፡-

ሀ) በተዋዋዮች ስምምነት በተገለፀው ጊዜ ውስጥ፣

ለ) ተዋዋዮች በመረጡት የግልግል ዳኝነት ማዕከል ሥነሥርዐት በተደነገገው ጊዜ ውስጥ፣ወይም

ሐ) የተዋዋዮች ስምምነት በሌለ ጊዜ ጉባዔዉ በወሰነዉ ጊዜ ውስጥ፣

መቅረብ ይኖርበታል፡፡

3/ ተከሳሽ በክስ አቤቱታ የተመለከቱትን ዝርዝር ፍሬ ነገሮች ባካተተ መልኩ መልሱን እና ደጋፊ ማስረጃ አዘጋጅቶ ያቀርባል፤

4/ መልስ የሚቀርብበት ጊዜ በተዋዋይ ወገኖች ወይም በግልግል ጉባዔዉ ባልተወሰነ ጊዜ ተከሳሽ ክሱ በደረሰዉ በሰልሳ ቀን ዉስጥ መልስ ማቅረብ አለበት፤

5/ በተዋዋይ ወገኖች የተደረገ ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በስተቀር ክስ ወይም መልስ በቀረበበት ጊዜ ማሻሻያዉን ያላደረገበትን ወይም ማስረጃውን ያላቀረበበት ምክንያት በቂ መሆኑን እና የግልግል ዳኝነት ሂደቱ የሚገኝበትን ደረጃ ከግምት በማስገባት ጉባዔው ተገቢ አይደለም ብሎ ካልከለከለ በስተቀር ማንኛውም ወገን ክሱን ወይም የክስ መልሱን በግልግል ዳኝነት ሂደት ሊያሻሽል እና ተጨማሪ ማስረጃዎችን ሊያይዝ ይችላል፡፡

## 33. <u>የቃልና የጽሑፍ ክርክሮች</u>

1/ ተከራካሪ ወገኖች ያደረጉት ስምምነት እንደተጠበቀ ሆኖ የቃል ክርክርን የመስማት ወይም ክርክሩን በሰነድ ወይም በሌሎች ግዙፍ ማስረጃዎች ላይ ተመሥርቶ ተገቢውን የማድረግ ሥልጣን የጉባዔው ይሆናል፤

2/ ተከራካሪ ወገኖች የቃል ክርክር ቀሪ እንዲሆን ካልተስማሙ በስተቀር ጉባዔው ስለክርክሩም ሆነ ስለማስረጃ አቀራረብ ከወሰነ በኋላ ለተከራካሪ ወገኖች በቂ የመዘጋጃ ጊዜ መስጠት አለበት፤የቃል ክርክር እንዲደረግ ከጠየቁ ጉባዔዉ የቃል ክርክሩን በተገቢዉ ወቅት ማካሄድ አለበት፤

3/ አንዱ ወገን በክርክር ጊዜ ለጉባዔው የሚሰጣቸው መግለጫዎች፣ ሰነዶችና ሌሎች ማስረጃዎች ሁሉ ለሌላ ተከራካሪ ወገንም ወዲያውኑ ሊደርሱት ይገባል፤ በተመሳሳይ ሁኔታ ጉባዔው ለውሳኔው መሠረት የሚያደርጋቸው የባለሙያ አስተያየት ለተከራካሪ ወገኖች ሊደርሱ ይገባል፡፡

## 34. የተከራካሪ ወገን መቅረት

በተዋዋይ ወገኖች የተደረገ የተለየ ስምምነት ከሌለ በስተቀር ፡-

1/ ከሳሽ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ (1) በተደነገገው መሠረት ክሱን ያላቀረበ እንደሆነ የግልግል ዳኝነት ጉባዔው መዝገቡን ይዘጋዋል፤

2/ ተከሳሽ በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት የመከላከያ መልሱን ያላቀረበ እንደሆነ ጉባዔው ተከሳሹ የከሳሽን ክስ እንዳመነ ሳይቆጥር የዳኝነት ሂደቱን ይቀጥላል፤

3/ ክርክር በሚሰማበት ጊዜ ከሳሽ ካልቀረበ እና በቀረበው ክስ ላይ ተከሳሽ ካመነ ባመነበት ላይ ጉባዔው ውሳኔ ይሰጣል፣ ተከሳሽ ክሱን ክዶ የተከራከረ እንደሆነ መዝገቡን ይዘጋዋል፤

4/ ማንኛውም ተዋዋይ ወገን በአካል ካልቀረበ ወይም ሰነዶችን ያላቀረበ እንደሆነ ጉባዔው የግልግል ዳኝነት ሂደቱን መቀጠል እና በቀረበለት መረጃ ላይ ተመሥርቶ ውሳኔ መስጠት ይችላል፤

5/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) ቢኖርም ተዋዋይ ወገን በአካል ያልቀረበው ወይም ማስረጃዎች ያላቀረበው በበቂ ምክንያት መሆኑን ጉባዔው ሲረዳ የተካሄዱ ሂደቶች ቀሪ እንዲሆኑ ፤ሂደቱ ወደ ኋላ እንዲመለስ ወይም ማስረጃዎቹን እንዲያቀርብ ሊፈቅድ ይችላል፤

6/ ቀጠሮውን አክብሮ ለመጣው ወገን ጉባዔው በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዐት ሕጉ መሠረት ወጪ እና ኪሳራይወስናል ፡፡

## 35. ባለሙያ ስለመሰየም

1/ በተዋዋይ ወገኖች የተደረገ የተለየ ስምምነት ከሌለ በስተቀር ጉባዔው፡-

ሀ) ሙያዊ ማብራሪያ ሊሰጥ የሚችል አንድ ወይም ከዚያ በላይ ሙያተኛ ሊሰይም ይችላል፣

ለ) ማንኛውም ተዋዋይ ወገን ለሙያተኛው አግባብነት ያለውን መረጃ እንዲሰጥ ወይም ሙያተኛው አግባብነት ያላቸውን ሰነዶች፣ ዕቃዎች ወይም ሌሎች ንብረቶች እንዲፈትሽ ወይም እንዲመረምር ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር መጠየቅ ይችላል፡፡

2/ በተዋዋይ ወገኖች የተደረገ የተለየ ስምምነት ከሌለ በስተቀር፣ በተዋዋይ ወገኖች በሚቀርብ ጥያቄ ወይም ጉባዔዉ በራሱ ተነሳሽነት ሙያተኛ መቅረብ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሙያተኛው ሙያዊ ማብራሪያውን በጽሑፍ፣ በቃል ወይም በማናቸውም ዘዴ ለጉባዔው ካቀረበ በኋላ በዳኝነት ሂደቱ ላይ ተገኝቶ በተዋዋይ ወገኖች ለሚቀርብለት ጥያቄ ምላሽ እንዲሰጥ በጉባዔዉ ሊታዘዝ ይችላል፤

3/ ተዋዋይ ወገን የቀረበውን የሙያ ምስክር በሚሰጠው ምስክርነት ላይ ሙያዊ ብቃቱን፣ ገለልተኛነቱን እና ነፃነቱን ለመቃወም ይችላል፡፡

**36. ማስረጃን ለመቀበል የፍርድ ቤት ድጋፍ**

1/ ጉባዔው በራሱ ወይም አንዱ ተከራካሪ ወገን የሚያቀርብለትን ጥያቄ መነሻ በማድረግ፣ ማስረጃዎችን መቀበልና ሌሎች የጉባዔውን ትዕዛዝ ለማስፈፀም ጉባዔው በራሱ ሥልጣን ሊፈፅማቸው የማይችሉ ወይም መፈፀም ካልቻለ ጉዳዩን ለማየት የሥረ ነገር ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት አማካኝነት እንዲፈፀምለት ጥያቄውን ማቅረብ ይችላል፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ጥያቄ የቀረበለት ፍርድ ቤት ጥያቄውን ሕግን መሠረት በማድረግ ዉድቅ ካላደረገዉ በስተቀር ማስረጃውን ይሰማል ወይም እንዲሰማ ትዕዛዝ ይሰጣል፣ ውጤቱንም በጽሑፍ ለጉባዔው ያሳውቃል፤

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ፍርድ ቤት እንደ አስፈላጊነቱ ጉባዔውና ተዋዋይ ወገኖች ማስረጃዎቹን በመስማት ሂደት እንዲሳተፉ ሊያደርግ ይችላል፡፡

**37. የጉዳዩን ሂደት በጽሑፍ ስለማስፈር**

1/ ጉባዔው የዳኝነት ሂደቱን በጽሑፍ ማስፈር አለበት፣ ተከራካሪ ወገኖች ወይም የግልግል ሂደቱ ተሳታፊዎች ሀሳባቸው ተሟልቶ ካልተጻፈ ወይም ስህተት ያለበት መሆኑን ካመኑ እንዲስተካከል መጠየቅ ይችላሉ፤

2/ የቀረበው የማስተካከያ ጥያቄ ተቀባይነት ማግኘት አለማግኘቱ በመዝገብ መስፈር አለበት፡፡

3/ መዝገቡ በግልግል ዳኞች በየገፁ መፈረም እና ማሕተም መደረግ አለበት፤ ሆኖም የግልግል ዳኝነት ጉባዔ በጊዜያዊነት ከተቋቋመና የራሱ ማሕተም ከሌለው የግልግል ዳኞች ፊርማ ይሆናል፡፡

**38. ምስጢራዊነት**

1/ በሕግ ወይም በስምምነት በሌላ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር፣ የጉባዔው የሥራ ሂደት እና ውሳኔ ምስጢራዊነት መጠበቅ አለበት፤

2/ የዕርቅ ስምምነቱን ለማስፈጸም መግለጹ አስፈላጊ ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር የዕርቅ ስምምነቱ ምስጢራዊነቱ የተጠበቀ ይሆናል፡፡

**39. የሦስተኛ ወገኖች ጣልቃ ገብነት እና ተጠሪነት**

1/ በግልግል ዳኝነት ዉሳኔዉ ጥቅማቸዉ ሊነካ የሚችሉ ሦስተኛ ወገኖች ከዉሳኔ በፊት አቤቱታቸዉን ለጉባዔዉ በማቅረብ ወደ ግልግል ዳኝነት ሂደቱ መግባት ይችላሉ፤

2/ ተዋዋይ ወገኖች ለኃላፊነታቸዉ ሦስተኛ ወገን እንዲጠየቅላቸዉ ወይም ካሳ እንዲከፍላቸዉ በማሰብ ሦስተኛ ወገኖች በሂደቱ እንዲገቡ ለጉባዔዉ ማመልከት ይችላሉ፤

3/ በዚህ አንቀጽ መሠረት ሦስተኛ ወገኖች ወደ ሂደቱ መቀላቀል የሚችሉት ሦስተኛ ወገኖችን ጨምሮ ተዋዋይ ወገኖችም ፍቃደኝነታቸዉን ሲገልጹ ብቻ ይሆናል፡፡

## ክፍል ስድስት

## የግልግል ዳኝነት ውሳኔ እና የሂደቱ መቋረጥ

### 40. በጉዳዩ ላይ ተፈፃሚ ስለሚሆኑ መሠረታዊ ሕጎች

1/ አለም አቀፍ በሆኑ የግልግል ዳኝነት ጉዳዮች ላይ ተዋዋይ ወገኖች ተፈፃሚ እንዲሆን የመረጡትን መሰረታዊ ሕግ ጉባዔው የመጠቀም ግዴታ አለበት፤

2/ ግልጽ የሆነ ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በስተቀር በተዋዋይ ወገኖች የሚደረግ የትኛዉም የሕግ ምርጫ ስምምነት ከጉዳዩ ጋር የተገናኘዉን የሌላ ሀገር መሠረታዊ ሕግ እንጂ የግጭት ሕግ እንዳልሆነ ይገመታል፤

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በስምምነት የተመረጠ ሕግ ከሌለ ጉባዔው ከጉዳዩ ጋር ቅርበትና አግባብነት ያላቸዉን ሕጎች በመምረጥ ተፈፃሚ ያደርጋል፤

4/ ጉዳዩ ዓለም ዓቀፍ የግልግል ዳኝነት ይዘት የሌለዉ ከሆነ ጉባዔዉ የኢትዮጵያን ሕግ ብቻ ተፈፃሚ ያደርጋል፤

5/ በርትዕ ወይም የታወቁ የንግድ ልምዶችን መሠረት በማድረግ ዉሳኔ መስጠት የሚቻለዉ ተዋዋይ ወገኖች ለጉባዔዉ ይህንን ዓይነት ስልጣን በግልጽ ከሰጡ ወይም ተፈፃሚው ሕግ ይህን ለማድረግ ሥልጣን የሚሰጠው ከሆነ ብቻ ነዉ፡፡

### 41. ከአንድ በላይ በሆኑ የግልግል ዳኞች ስለሚሰጥ ውሳኔ

1/ በተዋዋይ ወገኖች የተደረገ የተለየ ስምምነት ከሌለ በስተቀር ቁጥራቸው ከአንድ በላይ በሆኑ የግልግል ዳኞች የሚሰጥ ማንኛውም ውሳኔ የሚሰጠው በድምፅ ብልጫ ነው፤ በልዩነት የተሰጠ ሓሳብ ቢኖር ልዩነቱ ይመዘገባል፤

2/ ተዋዋይ ወገኖች በሌላ ሁኔታ ካልተስማሙ በስተቀር የግልግል ዳኝነት ውሳኔ ላይ ከግልግል ዳኞቹ መካከል በግልግል ውሳኔው ላይ ድምፅ ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆነ ይህንኑ ለተዋዋይ ወገኖች በማሳወቅ የተቀሩት የግልግል ዳኞች ውሳኔ ይሰጣሉ፤

3/ ተዋዋይ ወገኖች ወይም በቀሪዎቹ የግልግል ዳኞች ስልጣን የተሰጠው ሥነ ሥርዐታዊ ጉዳዮችን በሚመለከት ጉባዔዉ ሳይሟላ ትዕዛዞችን ሊሰጥ ይችላል፡፡

### 42. በስምምነት መሠረት ስለሚሰጥ የግልግል ውሳኔ

1/ በግልግል ዳኝነት በተያዘው ጉዳይ ላይ ተዋዋይ ወገኖች ዉሳኔ ከመሰጠቱ አስቀድሞ በሚደርሱት የጋራ መግባባት አለመግባባታቸው የተፈታ እንደሆነ የግልግል ዳኝነት ሂደቱ ይቋረጣል፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ተዋዋይ ወገኖች የደረሱበት ስምምነት በጉባዔው እንዲመዘገብላቸው ጥያቄ ካቀረቡ እና ውሳኔው የሕዝብን ሞራልና ፀጥታ የማይቃረን ከሆነ አለመግባባቱ የተፈታበት ጉዳይ እንደ ግልግል ጉባዔው ውሳኔ ተቆጥሮ በግልግል ጉባዔው መዝገብ ላይ ሊመዘገብ ይችላል፤ ውሳኔው በተያዘው ጉዳይ ላይ እንደማንኛውም በጉባዔ የተሰጠ ውሳኔ ሕጋዊ ውጤት ይኖረዋል፡፡

## 43. የግልግል ዳኝነት ውሳኔ ፎርም፣ይዘት እና ውጤት

1/ የግልግል ዳኝነት ውሳኔው በጽሑፍ ሆኖ በግልግል ዳኛው ወይም በግልግል ዳኞቹ መፈረም አለበት፡፤ከሁለት በላይ የሆኑ የግልግል ዳኞች በተሰየሙበት የግልግል ጉባዔ የሚሰጥ ውሳኔ በአብላጫው ዳኞች መፈረሙ በቂ ሆኖ ያልፈረመ ዳኛ ቢኖር ምክንያቱ መገለጽ ይኖርበታል፤

2/ ተዋዋይ ወገኖች ምክንያቱ እንዳይገለጽ ያደረጉት ስምምነት ከሌለ በስተቀር ወይም ውሳኔው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 42 መሠረት በጋራ መግባባት ላይ ተመሥርቶ የተሰጠ ካልሆነ በስተቀር ለዉሳኔዉ መሠረት የሆነው ምክንያት በግልግል ዳኝነት ጉባዔ መዝገብ መስፈር ይኖርበታል፤

3/ ውሳኔው የግልግል ጥያቄውን፣ የአለመግባባቱን ፍሬ ነገር፣ የተዋዋይ ወገን ስም፣ የዳኖቹ ስም፣አድራሻ እና እንደአ ስፈላጊነቱ ዜግነት፣ ለዉሳኔዉ መሠረት የሆነው ምክንያት፣የግልግል ዳኝነቱን ወጪ አከፋፈል፣ የተሰጠበትን ቀን እና በዚህ አዋጅ አንቀጽ 29 በተደነገገው መሠረት የግልግል መቀመጫ ቦታን መግለጽ አለበት፤

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት በዳኞች የተፈረመ የውሳኔ ግልባጭ ለእያንዳንዱ ተዋዋይ ወገን ውሳኔው በተፈረመ በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ እንዲደርስ ይደረጋል፤

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 የተደነገገው ቢኖርም፣ የግልግል ዳኝነት ጉባዔው የዳኝነቱን ሙሉ ክፍያ እና ወጪ በውሳኔው መሠረት እስኪከፈል ድረስ የውሳኔውን ግልባጭ ላልከፈለው ተዋዋይ ወገን እንዲሰጥ አይገደድም፤

6/ ማንኛውም የግልግል ዳኝነት ጉባዔ የሚሰጠው ውሳኔ በፍርድቤት እንደተሰጠ ፍርድ ይቆጠራል፤ በተዋዋይ ወገኖች ላይ አስገዳጅ እና በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ ክስ ከማቅረብ ይከለክላል፡፡

## 44. የግልግል ዳኝነትን ስለማቋረጥ

1/ የግልግል ዳኝነት ሂደት በሚከተሉት ምክንያቶች ሊቋረጥ ይችላል፡-

ሀ) የግልግል ዳኝነት ዉሳኔ መስጠቱ ለተከሳሽ አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር ክስ አቅራቢው ክሱን ሲያነሳ ወይም፣

ለ) ተዋዋይ ወገኖች ዳኝነቱ እንዲቋረጥ ሲስማሙ ፣

ሐ) የግልግል ዳኝነት ጉባዔው የዳኝነት ሂደቱን ማስቀጠል አስፈላጊ ሆኖ ካላገኘው ወይም ሂደቱን ለማስቀጠል የማያስችል በቂ ሁኔታሲኖር፣

መ) በሌሎች ሕጎች በግልፅ በተደነገጉ በማናቸውም ሌሎች ሁኔታዎች፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የግልግል ዳኝነቱ ሲቋረጥ ወጭውን በሚመለከት ጉባዔው ይወስናል፡፡

## 45. የግልግል ዳኝነት ወጭ

1/ ተዋዋይ ወገኖች በሌላ ሁኔታ ካልተስማሙ በስተቀር ለግልግል ዳኝነት የሚያስፈልገውን ወጪ እና የግልግል ዳኞች አገልግሎት ክፍያን ጨምሮ ጉባዔው በወጭው አከፋፈል ላይ ሊወስን ይችላል፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በጉባዔው የተሰጠ ውሳኔ ላይ ለመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት አቤቱታ ማቅረብ ይቻላል፡፡

## 46. ስለማረም፣ መተርጎም እና ተጨማሪ ውሳኔ

1/ በተዋዋይ ወገኖች የተደረገ የተለየ ስምምነት ከሌለ በስተቀር፣ አንድ ተከራካሪ ወገን የግልግል ዳኝነት ውሳኔ በደረሰው በ ሠላሳቀናት ውስጥ፡-

ሀ) አንደኛው ተዋዋይ ወገን ለሌላው ተዋዋይ ወገን በማሳወቅ በግልግል ጉባዔው ውሳኔ ላይ የአፃፃፍ ስህተት፣ የቁጥር አፃፃፍ ጉድለት ወይም ያልታሰበና ባለማስተዋል የተዘለለ የቃል ስህተት እንዲታረም መጠየቅ ይችላል፤

ለ) አንደኛው ተዋዋይ ወገን ለሌላው ተዋዋይ ወገን በማሳወቅ የግልግል ጉባዔው በተለየ የውሳኔው ጭብጥ ወይም ክፍል ላይ ትርጉም እንዲሰጥ መጠየቅ ይችላል፤

ሐ) አንደኛው ተዋዋይ ወገን ለሌላኛው ተዋዋይ ወገን በማሳወቅ ውሳኔው ለግልግል ጉባዔው ቀርቦ የተዘለለ የክሱ ክፍል ላይ ተጨማሪ ውሳኔ እንዲሰጥለት የግልግል ጉባዔውን መጠየቅ ይችላል፡፡

2/ የግልግል ጉባዔው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) መሠረት የቀረበውን ጥያቄ የተቀበለው እንደሆነ ጥያቄውን በተቀበለ በሠላሳ ቀናት ውስጥ እንደ ጥያቄው አግባብነት ያርማል ወይም ይተረጉማል፣ ጉባዔው ያደረገው ማስተካከያ ወይም የሰጠው ትርጓሜም የውሳኔው አካል እንደሆነ ይቆጠራል፡፤

3/ የግልግል ጉባዔው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ (ሀ) ላይ የተዘረዘሩት ስህተቶች መኖራቸውን ሲረዳ በራሱ ተነሳሽነት ውሳኔው በተሰጠ በ ሠላሳ ቀናት ውስጥ ማስተካከል ይችላል፤

4/ የግልግል ዳኝነት ጉባዔው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ (ሐ) መሠረት የቀረበውን ጥያቄ የተቀበለው እንደሆነ ጥያቄውን በተቀበለ በስልሳ ቀናት ውስጥ ተጨማሪ ውሳኔ ይሰጣል፣ የሚሰጠው ተጨማሪ ውሳኔ የቀድሞው የውሳኔው አካል እንደሆነ ይቆጠራል፤

5/ የግልግል ዳኝነት ጉባዔው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ማስተካከያ ለማድረግ፣ትርጓሜ ለመስጠት ወይም ተጨማሪ ውሳኔ ለማስተላለፍ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እና 4 የተመለከተውን ጊዜ ለተጨማሪ ሀያ ቀናት ሊያራዝመው ይችላል፤

6/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 43 የተመለከተው ማስተካከያ በማድረግ ፣ ትርጓሜ በመስጠት ወይም ተጨማሪ ውሳኔ በማስተላለፍ ላይም ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

## ክፍል ሰባት

## በግልግል ውሳኔ ላይ ስለሚቀርቡ አቤቱታዎች

## 47. የግልግል ዉሳኔን ስለመቃወም

1/ በግልግል ዳኝነት ሂደቱ ውስጥ የክርክር ተሳታፊ መሆን ሲገባው ያልተሳተፈና በተሰጠው የግልግል ውሳኔ መብቱ የተነካ ተዋዋይ ወገን ወይም ማንኛዉም ሦስተኛ ወገን የግልግል ውሳኔውን ወይም የዉሳኔዉን አፈፃፀም በመቃወም ጉዳዩ በግልግል ባይታይ ኖሮ ነገሩን ለማየት ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ውሳኔ መሰጠቱን ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ በስልሳ ቀን ዉስጥ መቃወሚያዉን ማቅረብ ይችላል፤

2/ መቃወሚያውን የሚያቀርበው ሦስተኛ ወገን አቤቱታውን አስቀድሞ ጉዳዩን ሲመለከተዉ ለነበረዉ ጉባዔ አቅርቦ በግልግል ዳኝነት ሂደቱ ጣልቃ ገብቶ ከነበረ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት መቃወሚያዉን ማቅረብ አይችልም፤

3/ የመቃወሚያ አቤቱታ አቅራቢዉ ከተዋዋይ ወገኖች መካከል ከሆነ ዉሳኔዉ ማሻሻያ እንዲደረግበት ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ወደ ጉባዔዉ ይመልሰዋል፤

4/ የመቃወሚያ አቤቱታ አቅራቢዉ ሦስተኛ ወገን ከሆነ ፍርድ ቤቱ የግልግል ዉሳኔዉን በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ሊሽረዉ ወይም ሊያሻሽለዉ ይችላል፤

5/ ፍርድን እና አፈፃፀምን ስለመቃወም በፍትሐብሔር ሥነሥርዐት ሕግ ዉስጥ የተደነገጉት ድንጋጌዎች ከዚህ አዋጅ ጋር እስካልተቃረኑ ድረስ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

## 48. ይግባኝ

1/ ተዋዋይ ወገኖች በግልግል ስምምነታቸው በተለየ ሁኔታ ካልተስማሙ በስተቀር በግልግል ውሳኔ ላይ ለፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ አይቻልም፤

2/ ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በስተቀር መሠረታዊ የሕግ ስህተት ሲኖር የሠበር አቤቱታ ማቅረብ ይቻላል፤

3/ ተቃራኒ ስምምነት ቢኖርም ተከራካሪ ወገኖች የግልግል ውሳኔው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ(5)፣ አንቀጽ 42፣ እና አንቀጽ 43/2/መሠረት በተሰጠ የግልግል ዳኝነት ውሳኔ ላይ ይግባኝ ማለት አይቻልም፤

4/ በግልግል ውሳኔ ላይ ይግባኝ የሚቀርበው ጉዳዩ በመደበኛ ፍርድ ቤት ታይቶ ቢሆን ኖሮ ጉዳዩን በይግባኝ ለማየት ስልጣን ላለዉ ፍርድ ቤት ነዉ፤ ይግባኙ የሚቀርበውም የግልግል ውሳኔው ለይግባኝ ባዩ በደረሰ በሰልሳ ቀናት ውስጥ ነው፤

5/ በፍትሐብሔር ሥነሥርዐት ሕግ ስለይግባኝ አቀራረብ የተመለከቱት አግባብ ያላቸው ድንጋጌዎች በግልግል ውሳኔ ላይ በሚቀርብ ይግባኝ ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ፤

6/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) መሠረት የይግባኝ ማመልከቻ የቀረበለት ፍርድ ቤት የግልግል ዳኝነት ዉሳኔዉን ከሰልሳ ቀን ላልበለጠ ጊዜ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዐት ሕጉ መሠረት አግዶ የማቆየት እና በይግባኙ ላይ ተገቢዉን የመወሰን ስልጣን ይኖረዋል፡፡

## 49. የግልግል ውሳኔን ስለመሻር

1/ በተዋዋይ ወገኖች የተደረገ ተቃራኒ ስምምነት ቢኖርም ተዋዋይ ወገኖች የግልግል ዳኝነት ዉሳኔዉ እንዲሻርላቸው ጉዳዩ በግልግል ዳኝነት ባይታይ ኖሮ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ማመልከት ይችላሉ፤

2/ የግልግል ዳኝነት ውሳኔ ለማሻር አቤቱታ ማቅረብ የሚቻለዉ ቀጥሎ በተዘረዘሩት ምክንያቶች ብቻ በአንዱ ሆኖ፣ ሁኔታው መኖሩን የማስረዳት ሸክሙ ወይም ኃላፊነት የአመልካቹ ይሆናል፡-

ሀ) አመልካቹ ላይ ተፈፃሚነት ባለዉ ሕግ መሠረት የግልግል ዳኝነት ዉል ለማድረግ የሚያስችለዉ ችሎታ የሌለው እንደሆነ፣

ለ) የግልግል ዳኝነት ስምምነቱ በተዋዋዮች በተመረጠዉ ሕግ ወይም በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ዋጋ የሌለውና ፈራሽ የሆነ ወይም ጊዜዉ ያለፈ እንደሆነ፣

ሐ) አቤቱታ አቅራቢው ዳኞች ስለመሾማቸዉ፣ ስለግልግል ዳኝነት ሂደት በቂ ማስታወቂያ ያልተሰጠው መሆኑን ሲያሳይ ወይም በሂደቱ ክርክሩን ለማሰማት አለመቻሉን ሲያስረዳ፣

መ) የግልግል ዳኞች በሂደቱ ገለልተኛነታቸዉን ወይም ነፃነታቸዉን ጠብቀዉ ዉሳኔ ያልሰጡ ሲሆን ወይም ከተዋዋይ ወገኖች መደለያ በመቀበል ዉሳኔ ሰጥተዉ ከሆነ፤

ሠ) የግልግል ዳኝነት ውሳኔዉ የተሰጠበት ጉዳይ ከግልግል ዳኝነት ስምምነቱ ወሰን በላይ ሲሆንወይም ጉባዔው ከተሰጠው ሥልጣን ወሰን በላይ ዉሳኔ የሰጠ ከሆነ፤

ረ) የጉባዔዉ አመሰራረት እና በሂደቱ የተተገበረዉ ሥነ ሥርዐት ከተዋዋይ ወገኖች ስምምነት ወይም በዚህ አዋጅ ከተደነገገዉ የሚቃረን እና ዉሳኔዉ ላይ ተጽዕኖ ያሳደረ ከሆነ ነው፡፡

3/ አቤቱታው የሚቀርበውም የግልግል ውሳኔው ለአቤት ባዩ በደረሰ በሠላሳ ቀናት ውስጥ መሆን አለበ፤ ነገር ግን ዉሳኔዉ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤት ከተፈፀመ በኋላ ለማሻር የሚቀርብ አቤቱታ ተቀባይነት የለዉም፤

4/ ፍርድ ቤቱ የሚከተሉት ምክንያቶች መኖራቸዉን ሲያረጋግጥ የግልግል ዳኝነት ውሳኔውን ሊሽር ይችላል፡-

ሀ) በግልግል ዳኝነቱ ዉሳኔ ያረፈበት ጉዳይ በኢትዮጵያ የግልግል ዳኝነት ሕግ መሠረት በግልግል ዳኝነት መታየት የማይችል ሲሆን፣

ለ) የግልግል ዳኝነት ዉሳኔዉን እዉቅና መስጠት ወይም እንዲፈፀም ማድረግ በሕዝብ ሞራል፣ ፖሊሲ ወይም ፀጥታ ላይ ችግር የሚፈጥር ከሆነ ፡፡

5/ የማሻር አቤቱታዉ የቀረበለት ፍርድ ቤት በአቤቱታዉ ላይ ዉሳኔ እስኪሰጥ ድረስየግልግል ዳኝነት ዉሳኔዉን በፍትሐብሔር ሕጉ መሠረት ከስልሳ ቀን ላልበለጠ ጊዜ አግዶ ለማቆየት ይችላል፤

6/ ለአቤቱታ መንስዔ የሆነዉን ምክንያት ከግምት ዉስጥ በማስገባት ፍርድ ቤቱ ውሳኔው በሙሉ ወይም በከፊል ሳይፈጸም ለማቆየት የዕግድ ትዕዛዝ በመስጠት ጉዳዩን መጀመሪያ ወደታየበት ጉባዔ ሊመልሰው ይችላል፤

7/ የቀረበዉ አቤቱታ ተቀባይነት ካገኘ እና ዉሳኔዉ ሙሉ በሙሉ ከተሻረ የግልግል ዳኝነት ዉሳኔዉ ዋጋ እንደሌለዉ ተቆጥሮ ቀሪ ይሆናል፡፡

8/ በመሻር አቤቱታዉ ላይ በፍርድ ቤት የተሰጠ ዉሳኔ ይግባኝ አይቀርብበትም፡፡

## ክፍል ስምንት

## <u>የግልግል ዳኝነት ጉባዔ ውሳኔን እውቅና ስለመስጠትና ስለማስፈጸም</u>

### 50. <u>የግልግል ዳኝነት ጉባዔን ውሳኔ ስለማስፈጸም</u>

1/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ 49 ወይም 51 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በኢትዮጵያም ሆነ በውጭ ሀገር የተሰጠ የግልግል ዳኝነት ውሳኔ አስገዳጅ እንደሆነ ተቆጥሮ ጉዳዩ በፍርድ ቤት ቢታይ ኖሮ ፍርዱን ሊያስፈፅም ለሚችለው ፍርድ ቤት በማቅረብ በፍትሐብሔር ሥነሥርዐት ሕግ የፍርድ ውሳኔ በሚፈፀምበት አኳኋን ይፈጸማል፤

2/ የግልግል ዳኝነት ውሳኔ በፍርድ ቤት እንዲፈፀምለት የሚፈልግ ወገን የግልግል ስምምነቱን፣የውሳኔውን ዋና ቅጅ ወይም ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ የውሳኔ ግልባጭ ማቅረብ ይኖርበታል፤

3/ ከውጭ ሀገር ለእዉቅና ወይም አፈፃፀም ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡ የግልግል ውሳኔዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከቱት እንደተጠበቁ ሆነው በሚመለከተው አካል የተረጋገጡ ሰነዶች መቅረብ ይኖርባቸዋል፤

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የግልግል ዳኝነት ውሳኔ የተሰጠበት ቋንቋ ከአፈፃፀም ፍርድ ቤቱ የስራ ቋንቋ የተለየ ሲሆን አመልካቹ በፍርድ ቤቱ የሥራ ቋንቋ አስተርጉሞ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

## 51. የግልግል ዉሳኔ እንዳይፈፀም ስለመቃወም

1/ የግልግል ዳኝነት ዉሳኔ እንዳይፈፀም መቃወም የሚቻለዉ ከዚህ በፊት ዉሳኔዉ እንዲሻር ለፍርድ ቤት አቤቱታ ቀርቦ ዉድቅ ያልተደረገ ከሆነ ነው፤

2/ የግልግል ዳኝነት ዉሳኔ እንዳይፈፀም መቃወም የሚቻለዉ በሚከተሉት ምክንያቶች ብቻ ነዉ፡-

ሀ) *ፍርዱን በተቃወመው ወገን ላይ ተፈፃሚነት ባለዉ ሕግ መሠረት የግልግል ዳኝነት ዉል ለማድረግ የሚያስችል ችሎታ የሌለው እንደሆነ፣ ወይም የግልግል ዳኝነት ስምምነቱ እንዲገዛበት በተዋዋዮች በተመረጠዉ ሕግ መሠረት ወይም የተዋዋዮች ስምምነት ከሌለ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ዋጋ የሌለውና ፈራሽ የሆነ ወይም ጊዜዉ ያለፈ እንደሆነ፤*

ለ) አቤቱታ አቅራቢው ዳኞች ስለመሾማቸዉ፣ ስለግልግል ዳኝነት ሂደት በቂ ማስታወቂያ ያልተሰጠው መሆኑን ሲያሳይ ወይም በሂደቱ ክርክሩን ለማሰማት አለመቻሉን ሲያስረዳ፤

ሐ) የግልግል ዳኞች በሂደቱ ገለልተኛነታቸዉን እና ነፃነታቸዉን ጠብቀዉ ዉሳኔ ያልሰጡ ሲሆን ወይም ከተዋዋይ ወገኖች መደለያ በመቀበል ዉሳኔ ሰጥተዉ ከሆነ፤

መ) የግልግል ዳኝነት ውሳኔዉ የተሰጠበት ጉዳይ ከግልግል ዳኝነት ስምምነቱ ወሰን በላይ ሲሆን፣ ወይም ጉባዔው ከተሰጠው ሥልጣን ወሰን በላይ ዉሳኔ የሰጠ እንደሆነ ፤፣

ሠ) የጉባዔዉ አመሰራረት እና በሂደቱ የተተገበረዉ ሥነሥርዐት ከተዋዋይ ወገኖች ስምምነት ወይም በዚህ አዋጅ ከተደነገገዉ የሚቃረን እና ዉሳኔዉ ላይ ተፅዕኖ ያሳደረ ከሆነ፤

ረ) የግልግል ዳኝነት ዉሳኔዉ የመጨረሻ ዉሳኔ ደረጃ ላይ ያልደረሰ ከሆነ፣ የተሻረ ወይም ዉሳኔዉ የታገደ ከሆነ::

3/ ፍርድ ቤቱ የሚከተሉት ምክንያት መኖሩን ሲያረጋግጥ፡- የግልግል ዳኝነት ውሳኔውን ሊሽር ይችላል፡-

ሀ) በግልግል ዳኝነቱ ዉሳኔ ያረፈበት ጉዳይ በዚህ ሕግ መሠረት በግልግል ዳኝነት መታየት የማይችል ሲሆን፣

ለ) የግልግል ዳኝነት ዉሳኔዉን እዉቅና መስጠት ወይም እንዲፈፀም ማድረግ በሕዝብ ሞራል፣ ፖሊሲ ወይም ፀጥታ ላይ ችግር የሚፈጥር ከሆነ፡፡

4/ ፍርድ ቤቱም ዉሳኔዉ እንዲፈፀም ወይም እንዳይፈፀም የፍርድ ባለመብቱ ጥያቄ ባቀረበ ጊዜ የፍርድ ባለዕዳዉ በቂ ዋስትና እንዲያቀርብ ትዕዛዝ በመስጠት ነገሩን ለማጣራት ቀጠሮ ሊሰጥ ይችላል፤

5/ የግልግል ዉሳኔ እንዳይፈፀም የቀረበ ተቃዉሞ ላይ በፍርድ ቤት የተሰጠ ዉሳኔ ይግባኝ አይቀርብበትም፡፡

## 52. *በውጭ ሀገር የተሰጠ የግልግል ዳኝነት ውሳኔን እውቅና ስለመስጠት እና ማስፈፀም*

1/ በዉጭ ሀገር የተሰጠ የግልግል ዳኝነት ዉሳኔ ኢትዮጵያ ባፀደቀቻቸዉ አለም አቀፍ ስምምነቶች የሚወድቅ ከሆነ በስምምነቱ መሠረት እዉቅና ሊሰጠዉ ወይም ሊፈፀም ይችላል፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በውጭ ሀገር የተሰጠ የግልግል ዳኝነት ውሳኔ እዉቅና ላይሰጠዉ ወይም ላይፈፀም የሚችለዉ በሚከተሉት ምክንያቶች ብቻ ነዉ፡-

ሀ) የእንካ ለእንካ መርህን መሠረት ያላደረገ ሲሆን፣

ለ) የግልግል ዳኝነት ውሳኔው በማይፀና የግልግል ዳኝነት ስምምነት መሠረት ወይም ዉሳኔዉ የተሰጠበት ሀገር ሕግ በሚፈቅደዉ መሠረት ባልተቋቋመ ጉባዔ የተሰጠ እንደሆነ፣

ሐ) የተሰጠው ውሳኔ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረትሊፈፀም የማይችል እንደሆነ፣

መ) ተዋዋይ ወገኖች የግልግል ዳኞችን ለመምረጥ እኩል መብት ያልነበራቸዉ እንደሆነ ወይም በክርክሩ ላይ ማስረጃቸውን ለማቅረብና ክርክራቸውንም ቀርቦ ለማሰማት እኩል መብት ያልነበራቸዉ እንደሆነ፣

ሠ) ዉሳኔ የተሰጠበት ጉዳይ በኢትዮጵያ ሕግ በግልግል ዳኝነት ሊታይ የማይችል እንደሆነና፣

ረ) የውሳኔውም አፈፃፀም የሕዝብን ፓሊሲ፣ ሞራልና ፀጥታ የሚቃረን እንደሆነ፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሠረት የውሳኔ ይፈፀምልኝ ማመልከቻ የሚቀርበው ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይሆናል፡፡

# ክፍል ዘጠኝ

## *ስለ ዕርቅ*

## 53. *የዕርቅ ሥርዐት አጀማመር*

1/ እንታረቅ ባይ ወገን ለዕርቁ መነሻ የሆነውን ጉዳይ በመጥቀስና ምላሽ የሚጠበቅበትን ቀን በመወሰን ለሌላኛው ወገን የዕርቅ ሓሳቡን በቃል ወይም በጽሑፍ ያሳውቀዋል፤

2/ የዕርቅ ሓሳቡን ሌላኛው ወገን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው ጊዜ ውስጥ መቀበሉን የገለፀ እንደሆነ የዕርቅ ሂደቱ ይጀመራል፤

3/ እንታረቅ ባይ ወገን ሌላኛው ወገን ማስታወቂያው በደረሰው በሠላሳቀናት ወይም ምላሽ የሚሰጥበት ቀን እንዳበቃ የዕርቅ ሓሳቡን ለመቀበል እንዳልፈለገ በመቁጠር የዕርቅ ሓሳቡን እንዳነሳ ለሌላኛው ወገን ያሳውቀዋል፡፡

## 54. <u>የአስታራቂዎች ብዛት</u>

1/ ተዋዋይ ወገኖች ሁለት ወይም ከዚያ በላይ አስታራቂዎች እንዲኖሩ በተለየ አኳኋን ካልተስማሙ በስተቀር የዕርቅ ሂደት በአንድ አስታራቂ ይመራል፤

2/ የአስታራቂዎች ቁጥር ከአንድ በላይ የሆነ እንደሆነ አስታራቂዎቹ በጋራ መስራት ይኖርባቸዋል፡፡

## 55. <u>አስታራቂን ስለመሰየም</u>

1/ ተዋዋይ ወገኖች የተለየ ሥነ ሥርዐት እንዲኖር ካልተስማሙ በስተቀር፣በአስታራቂ ብዛት እና ማንነት ላይ ለመስማማት ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል፤

2/ ተዋዋይ ወገኖች አስታራቂ ሆኖ ለመሥራት ተስማሚ የሆነን ሰው እንዲጠቁሟቸው ወይም አስታራቂ በቀጥታ እንዲሰይምላቸው የአንድን ተቋም ወይም የግለሰብ እገዛ መጠየቅ ይችላሉ፤

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት አስታራቂን ለመጠቆም ወይም ለመሰየም ጥያቄ የቀረበለት ተቋም ወይም ግለሰብ የአስታራቂውን ነፃነት፣ገለልተኛነት እና አንደ አግባብነቱ አስታራቂው ከተዋዋይ ወገኖች የተለየ ዜግነት ያለው ስለመሆኑ ከግምት ማስገባት ይኖርበታል፤

4/ አስታራቂው ለአስታራቂነት ሲመረጥ ወይም በአስታራቂነት ከተሰየመበት ጊዜ አንስቶ በማስታረቁ ሂደት የሚያጋጥሙትን በነፃነቱ እና በገለልተኛነቱ ላይ ምክንያታዊ ጥርጣሬ ያሳድራሉ ብሎ የሚገምታቸውን ማናቸውንም አካባቢያዊ ሁኔታዎች ሳይዘገይ ለተዋዋይ ወገኖች መግለጽ ይኖርበታል፡፡

## 56. <u>የዕርቅን ጉዳይ ለአስታራቂ ስለማቅረብ</u>

1/ አስታራቂው እንደተሰየመ ተዋዋይ ወገኖች ስለ ዕርቁ ጉዳይ አጠቃላይ ሁኔታ እና የዕርቁን ፍሬ ነገር በጽሑፍ እንዲያሳውቁት ሊጠይቅ ይችላል፣ እያንዳንዱ ተዋዋይ ወገን ለአስታራቂው ያቀረበውን ተጨማሪ የጽሑፍ መግለጫ ቅጂ ለሌላው ወገን እንዲደርሰው ማድረግ አለበት፤

2/ አስታራቂው ተዋዋይ ወገኖችን ጉዳዩን ያጠናክሩልኛል የሚሏቸውን እውነታዎች በሰነዶች እና በሌሎች ማስረጃዎች አስደግፎ በተጨማሪነት በጽሑፍ እንዲያቀርብ ሊጠይቅ ይችላል፤

3/ አስታራቂው በየትኛውም የዕርቅ ሂደት አግባብነት አላቸው የሚላቸውን ተጨማሪ ማስረጃዎች እንዲቀርቡለት ማንኛውንም ተዋዋይ ወገን ሊጠይቅ ይችላል፡፡

## 57. <u>ዕርቅ በሌሎችሕጐች እንዲመራ የማይገደድ ስለመሆኑ</u>

ተዋዋይ ወገኖች በተለየ ሁኔታ የሚያደርጉት ስምምነት እንደተጠበቀ ሆኖ ዕርቅ በሌሎች መሠረታዊም ሆነ ሥነሥርዐታዊ ሕጐች መሠረት እንዲመራ አይገደድም፡፡

## 58. <u>የአስታራቂው ሚና</u>

1/ አስታራቂው ነፃና ገለልተኛ ሆኖ ተዋዋይ ወገኖች አለመግባባታቸውን በስምምነት እንዲፈቱ ማገዝ አለበት፤

2/ አስታራቂው ምክንያታዊነት እና ፍትሐዊነት መርሆዎችን መሠረት በማድረግ የተዋዋይ ወገኖችን መብት እና ግዴታ፤ ልማዳዊ አሠራር እና በተዋዋይ ወገኖች መካከል የነበረውን የቆየ የሥራ ወይም የንግድ ግንኙነት ጨምሮ አለመግባባቱን የሚመለከቱ አካባቢያዊ ሁኔታዎችን ከግምት ማስገባት አለበት፤

3/ አስታራቂው የጉዳዩን አካባቢያዊ ሁኔታ በቃል መሰማትን ጨምሮ የተዋዋይ ወገኖች ፍላጐት እና አለመግባባቱን በአጭር ጊዜ ውስጥ መፍታት አስፈላጊነት ግምት ውስጥ በማስገባት ተስማሚ መስሎ በታየው ሁኔታ ዕርቁን ሊመራ ይችላል፤

4/ አስታራቂው በየትኛውም የዕርቅ ደረጃ ላይ የዕርቅ ሓሣብ ሊያቀርብ ይችላል፤ የሚያቀርበው የዕርቅ ሓሣብ በጽሑፍ እንዲሆን እና ምክንያቱን እንዲገልጽ አይጠበቅበትም፡፡

## 59. አስተዳደራዊ ድጋፍ ስለ መጠየቅ

ዕርቁን ለማመቻቸት ተዋዋይ ወገኖች ወይም አስታራቂው የተዋዋይ ወገኖችን ፈቃድ ሲያገኝ ፣ አግባብነት ካለው ተቋም ወይም ግለሰብ አስተዳዳራዊ ድጋፍ መጠየቅ ይችላል፡፡

## 60. በአስታራቂው እና በተዋዋይ ወገኖች መካከል ስለሚደረግ ግንኙነት

1/ አስታራቂው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከተዋዋይ ወገኖች ጋር በጋራ ወይም በተናጠል በጽሑፍ ወይም በቃል ሊገናኝ ይችላል፤

2/ በተዋዋይ ወገኖች የተደረገ ስምምነት ከሌለ በስተቀር፣ አስታራቂው ከተዋዋይ ወገኖች ጋር በመመካከር እና የዕርቁን አካባቢያዊ ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት የሚገናኙበትን ቦታ ይወስናል፡፡

## 61. መረጃን ስለመግለጽ

1/ አስታራቂው ከአንደኛው ተዋዋይ ወገን አለመግባባቱን በሚመለከት ያገኘውን መረጃ ለሌላው ተዋዋይ ወገን ሊገልጽለት ይችላል፤

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ቢኖርም መረጃውን የሰጠው ወገን በምስጢር እንዲያዝለት የጠየቀ እንደሆነ አስታራቂው መረጃውን መግለጽ የለበትም፡፡

## 62. ተዋዋይ ወገኖች ከአስታራቂው ጋር ሊኖራቸው ስለሚገባ ትብብር

ተዋዋይ ወገኖች በቅን ልቦና ከአስታራቂው ጋር የመተባበር ፣ በአስታራቂው ሲጠየቁ ሰነዶችን እና ማስረጃዎችን የመስጠት እና በውይይት ጊዜ መገኘት ይኖርባቸዋል፡፡

## 63. በተዋዋይ ወገኖች የሚቀርብ የዕርቅ ሃሣብ

እያንዳንዱ ተዋዋይ ወገን በራሱ ተነሳሽነት ወይም ከአስታራቂው በሚቀርብለት ጥያቄ አለመግባባቱን ለመፍታት የሚያስችል አስታራቂ ሃሣብ ማቅረብ ይችላል፡፡

## 64. የዕርቅ ስምምነት

1/ አስታራቂው በተዋዋይ ወገኖች ዘንድ ተቀባይነት ሊኖረው የሚችል የዕርቅ ሓሳብ መኖሩን ሲያምን የማግባቢያ ሰነዱን አዘጋጅቶ ተዋዋይ ወገኖች እንዲያዩት ያደርጋል፤ በተዋዋይ ወገኖች የቀረብ ሃሣብ ካለ በቀረበው ሃሣብመሠረት የማግባቢያ ሰነዱን ሊያስተካክል ይችላል፤

2/ ተዋዋይ ወገኖች አለመግባባቱን ለመፍታት ከተስማሙ የዕርቅ ሰነድ በማዘጋጀት መፈራረም ይችላሉ፣አስታራቂው በተዋዋይ ወገኖች ጥያቄ ከቀረበለት፣ የዕርቅ ስምምነት ሰነዱን ራሱ ሊያዘጋጅ ወይም ተዋዋይ ወገኖች የሚያዘጋጁት ከሆነ ሊያግዝ ይችላል፤

3/ የዕርቅ ስምምነት ሰነዱ በተዋዋይ ወገኖች ሲፈረም በተዋዋይ ወገኖች እና በእነርሱ በኩል የሙብት ጥያቄ ባላቸው ሌሎች ሰዎች ላይ የመጨረሻ እና አስገዳጅነት ይኖረዋል፤

4/ አስታራቂው የዕርቅ ስምምነት ሰነዱን በማረጋገጥ ቅጂውን ለእያንዳንዱ ተዋዋይ ወገን መስጠት ይኖርበታል፡፡

## 65. የዕርቅ ስምምነት ውጤት እና አፈጻጸም

በዚህ አዋጅ በግልግል ዳኝነት ውሳኔ ውጤትና አፈጻጸም ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑት ድንጋጌዎች እንደ አግባቡ በዕርቅ ስምምነት ላይም ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

## 66. የዕርቅን ሂደት ስለማቋረጥ

የዕርቅ ሂደት በሚከተሉት ሁኔታዎች ይቋረጣል፤

1/ አስታራቂው ከተዋዋይ ወገኖች ጋር በመመካከር ዕርቁን መቀጠል አላስፈላጊ ሆኖ ማግኘቱን ሲያሳውቅ፣

2/ ተዋዋይ ወገኖች ዕርቁ መቋረጡን ለአስታራቂው በጽሑፍ ሲገልፁ፣ ወይም

3/ አንዱ ተዋዋይ ወገን ለሌላኛው ተዋዋይ ወገን እና ለአስታራቂው ዕርቁን ስለማቋረጡ በፅሑፍ ሲገልጽ፡፡

## 67. ለፍርድ ቤት ወይም ለግልግል ዳኝነት ስለማቅረብ

አስታራቂው ዕርቅ ስላለመደረጉ በፅሑፍ ካልገለጸ በስተቀር፣ ተዋዋይ ወገኖች በዕርቅ የተያዘውን ጉዳይ ፍርድ ቤት ወይም ወደ ግልግል ዳኝነት ማቅረብ አይችሉም፡፡

## 68. የዕርቅ ሂደት ወጪ እና ክፍያ

1/ በተዋዋይ ወገኖች የተደረገ የተለየ የውል ስምምነት ከሌለ በስተቀር አስታራቂው ለዕርቁ ያወጣውን ወጪ ለመሸፈን ካልሆነ በስተቀር ለአገልግሎቱ የሚከፈለው ክፍያ አይኖርም፤

2/ የዕርቁ ሂደት ሲቋረጥ አስታራቂው የዕርቅ ወጪ በመወሰን ለተዋዋይ ወገኖች በፅሑፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፤

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተው ወጪ የሚከተሉትን ያካትታል፡-

ሀ) በአስታራቂው እና በተዋዋይ ወገኖች ፈቃድ አስታራቂው ለጠራቸው ምስክሮች የሚከፈል ክፍያ እና ወጪ፣

ለ) በተዋዋይ ወገኖች ፈቃድ በአስታራቂው ጠያቂነት በሙያተኛ ለተሰጠ ሙያዊ አስተያየት ወይም ምክር የሚከፈል የአገልግሎት ክፍያ፣

ሐ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 55 እና አንቀጽ 59 መሠረት ለተሰጠአገልግሎት የሚከፈሉ ክፍያዎች፣

መ) ሌሎች ከዕርቅ ሂደት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ወጪዎች እና ክፍያዎች፡፡

4/ በተዋዋይ ወገኖች የተደረገ የተለየ ስምምነት ከሌለ በስተቀር፣ ወጪዎች እና ክፍያዎች በተዋዋይ ወገኖች በጋራ ይሸፈናሉ፤ ሆኖም ወጪው አንደኛውን ተዋዋይ ወገን ብቻ የሚመለከት ከሆነ ወጪው በዚሁ ተዋዋይ ወገን ይሸፈናል፡፡

## 69. ክልከላ

በተዋዋይ ወገኖች የተደረገ የተለየ ስምምነት ከሌለ በስተቀር ፡-

1/ አስታራቂው በዕርቅ በያዘው ጉዳይ በማንኛውም የግልግል ዳኝነት ወይም የፍርድ ሂደት ላይ የግልግል ዳኛ፣ ጠበቃ ወይም ወኪል በመሆን መሥራት፣

2/ በማንኛውም የግልግል ዳኝነት ወይም የፍርድ ሂደት ላይ በተዋዋይ ወገኖች ምስክር ሆኖ መቅረብ፣

የተከለከለ ነው፡፡

## 70. በማስረጃነት መቅረብ ስለማይችሉ ጉዳዮች

ተዋዋይ ወገኖች ከዚህ በታች የተመለከቱትን በግልግል ዳኝነት ወይም በፍርድ ሂደት በማስረጃነት ማቅረብ አይችሉም፡-

1/ አለመግባባቱን በዕርቅ ለመፍታት በማሰብ በአንደኛው ተዋዋይ ወገን የተሰጠ አስተያየት ወይም ሓሳብ፣

2/ በዕርቅ ሂደት በአንደኛው ተዋዋይ ወገን የተሰጠ የእምነት ቃል፣

3/ በአስታራቂው የቀረበ የዕርቅ ሓሳብ እና በአስታራቂው የቀረበውን የዕርቅ ሓሳብ ለመቀበል በአንደኛው ተዋዋይ ወገን የተሰጠ ፈቃደኝነት፡፡

## 71. የዳኝነት ክፍያ ስለመመለስ

1/ ተዋዋይ ወገኖች ጉዳያቸው በፍርድቤት እንዲታይ ክስ መስርተው ከነበረ እና ክሱን በመተው ጉዳያቸውን በዕርቅ ከጨረሱ ለፍርድቤት የከፈሉት የዳኝነት ክፍያ እንደአግባብነቱ ተመላሽ ይደረግላቸዋል፤

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ዝርዝር አፈፃፀም በሚኒስትሮች ምክርቤት በሚወጣ ደንብ ይወሠናል፡፡

# ክፍል አስር

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 72. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

1/ ይህ አዋጅ በስራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተፈረሙ የግልግል ዳኝነት ስምምነቶች አዋጁ ከመውጣቱ በፊት በነበሩ ሕጎች መሠረት የሚገዙ ይሆናል፤

2/ ይህ አዋጅ ስራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተጀመሩ የግልግል ዳኝነቶች ወይም የግልግል ዳኝነትን በተመለከተ በፍርድ ቤቶች በመታየት ላይ ያሉ ጉዳዮች ፣ የክርክር ሂደቶች እና የተሰጡ ውሳኔዎች አፈጻጸም ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት በነበሩ ሕጎች መሠረት ይታያሉ፤

3/ ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት የግልግል ዳኝነት ስምምነት የፈፀሙ ወይም በሂደት ላይ ያሉ ተዋዋይ ወገኖች በዚህ አዋጅ መሠረት ለመዳኘት መስማማት ይችላሉ፡፡

**73. <u>ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጐች</u>**

ከአንቀጽ 3318 እስከ 3346 የተደነገጉት እና ሌሎች የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች፣ይህን አዋጅ የሚቃረን ማናቸውም ሌላ ሕግ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ አዋጅ ውስጥ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

**74. <u>ደንብ የማውጣት ሥልጣን</u>**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

**75. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ .....ቀን 2012 ዓ.ም

ሳህለ ወርቅ ዘውዴ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊ ፕሬዚዳንት